
# በውስጥ ገፆች


ርእሰአንቀፅ ........................................................ገፅ2
እንግዳችን ........................................................ገፅ3
ግጥም ........................................................ገፅ7
አድዋናኢትዮጵዊነት ........................................................ገፅ9
አድዋየማይናወጥአለት ........................................................ገፅ10
አድዋናምርጫ ........................................................ገፅ13
እኔሴትነኘጦርነትአልወድም........................................ገፅ14





# የአድዋ ፖለቲካ አይደለም !!

ልክ የዛሬ 129 ዓመት መራር ተጋድሎ በአድዋ ተራሮች ላይ ተደረገ ፡፡ ዓላማውም የሰው ልጆች ሁሉ እኩል ሆነው የመቆጠር መብትን በተፃራሪው ለ ተግበር ባህር አቋርጦ ድንበር አልፎ የ መጣን የውጭ ባዕድ ሀይል ለመመከት ብሎም ወደ መጣበት ለመመለስ የተደረገ ቁርጠኝነት የታየበት፡፡ እልህ አስጨራሽ ተጋድሎ የተደረገበት ዘግናኝ ጦርነት ነበር፡፡
በዘመናዊ መልኩ (ወቅቱ በነበረው ስልጣኔ እና የእድገት ደረጃ የሚያሳይ ) የሰለጠነ ወታደር ፤ እስከ ፍንጫው መሳሪያ ታጥቆ የመጣ የጦር ኃይልን በጥቂት የነፍስ ወከፍ መሳሪያ ፤ በጨበጣ ውጊያ፤ በባህላዊ ሀገር በቀል ጦርና ጎራዴ ተገጥሞ ድል የተመታበት፤ሺዎች ወድቀው ሚሊዮኖች ቀና ያሉበት ፡፡በዘመን የማያረጅ በግዜ የማይጠወልግ ታላቅ ታሪክ የተፃፈበት እለት የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም አድዋ ፡፡

የአድዋው ጦርነት በተለይ በኢትዮጵያ በኩል በፈታኝ ወቅት የተደረገ እንደ ነበር በወቅቱ የነበሩ የአይን እማኞች በተባው ብዕራቸው ከትበው በማቆየታቸው ዛሬም ድረስ ከትውልድ ወደ ትውልድ ገድሉ ሲዘከር እንዲኖር አድርገዋል፡፡ በተለይ በተፈጥሮ አየር መዛባት ምክንያት በዝናብ ጥገኛ በነበረው የሀገሬው ሰው ላይ የተከሰተው ርሀብ የዜጎች ህልውና እስከወዲያኛው ማሽለብ በሆነበት በዛ ወቅት ጦርነት ሲታከልበት ውጤቱን ለመገመት ብዙም ተጨንቆና የታሪክና ድርሳን አገላብጦ ትንታኔ ለመስጠት ግዜ መግዛት አላስፈለገም ነበር፡፡ወራሪው የጣልያን ሰራዊት የጦር መኮንኖችም ቢሆኑ ከዚህ መላምት በመነሳት ያለምንም ጥርጥር ድሉ የነሱ እንደሚሆን በመመካት ሲናገሩ ነበር ፡፡

እርግጥ ነው ወቅቱ ለአፍሪካውያን መልካም የሚባል አልነበረም፡፡አውሮፓውያን በርሊን ላይ 1884-1885 ተሰብስበው በደረሱበት ስምምነት መነሻ መሰረት የአፍሪካ አህጉርን ተቀራመቱት። ዋይታና ጩኸት የበረታበት አድማጭ ጠፍቶ ጩኸቱ እንደ ገደል ማሚቱ የሚስተጋባበት ፤የወራሪዎች ጡጫ የበረታበት፤አውሮፓውያን የበላይነታቸው በአፍሪካ ምድር ላይ የተረጋገጠበትና የነገሰበት ስለነበር የኢትዮጵያም እጣ ክፍልም ከሌሎቹ ሀገራት የተለየ ይሆናል ብሎ የገመተ አልነበረም፡፡ ሆኖም በወቅቱ የጣሊያኖች ጭንቅላት ሊያስበው ከሚችለው በላይ በሚመጥቅ ብልሀት ልቀው የተገኙት ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ህዝባቸውን አስተባብረው ከጎናቸው በማሰለፍ ሊገዳደሩት አይደለም ሊያስቡት በሚከብድ ሁኔታ በእብሪት ተውጦ የመጣውን ሀይል በመረጠው መንገድ ገጠሙት፡፡

በተለያዩ ወቅቶች በተደረጉ ቅድመ አድዋ ጦርነቶች ኢትዮጵያውያንን ድል መንሳት የተሳነው የጣሊያን ሰራዊት ያለ የሌለ ሀይሉን አሰባስቦ አድዋ ላይ ከተመ ፡፡ንጉሱ አፄ ሚኒሊክም ከፊት በተደረጉ ጦርነቶች ኢትዮጵያውያንን ድል መንሳት የተሳነው የጣሊያን ጦር ሀገሬን ለቆ ይወጣል ብለው የማርያም መንገድ ሰጥተው ውስጣዊ ሀይላቸውን እያጠነከሩ ቢጠብቁም በጣሊያን በኩል የታየው ምላሽ ለዳግም ጦርነት የሚያነሳሳ ሆኖ በመገኘቱ ዙሪያ ገባውን ማጥራት ለዛም ይረዳቸው ዘንድ በዲፕሎማሲ እያለሳለሱ ክንዳቸውን ማጠናከር ተያያዙት፡፡በዚህም ለጣሊያን መረጃ ያቀብሉ የነበሩ የግል ጠባቂዎቻቸውን ሳይቀር መንጥረው በማውጣት ራሳቸውን በሰው ሀይልም በጦር መሳርያም አደራጁ፡፡ለጣሊያንም የተሳሳተ መረጃ እንዲደርሰው እያደረጉ ዘለቁ፡፡ በዚህ መረጃ ልቡ ያኮበኮበው ባሪያቴሪ የመጨረሻው ጦርነት እንዲደረግ የካቲት 22 ቀን 1888 ለ 23 አጥቢያ በ5 አቅጣጫ የማጥቃት ዘመቻ እንዲደረግ ትእዛዝ አስተላለፈ፡፡ንጉሱና ኢትዮጵያውያኑ አናብስት የሚፈልጉት ቀን ደረሰ፡፡በየአቅጣጫው የተሰለፈውን የጣሊያን ጦር አንዱ ለአንዱ እንዳይደራረሱ አድርገው ወጉት፡፡ የጣሊያን ጦር አድዋ ላይ በኢትዮጵያውያን አናብስቶች የሚደርስበትን ጥቃት መቋቋም ተስኖት የሽንፈት ፅዋውን በምሬት ተጎነጨ፡፡አዲስ ተስፋ አዲስ ብስራት በአፍሪካ ምድር በጥቁር ህዝቦች ልቡና ውስጥ ማቆጥቆጥ ጀመረ፡፡

አድዋ የድሎች ሁሉ በኩራት ሆኖ በባርነት ቀንበር ስር ያሉ ጥቁር ህዝቦች ለነፃነታቸው ዘብ እንዲቆሙ ፋና ወጊ ሆነ ፡፡ ጥቁር በግዞት ብቻ ሳይሆን በአሸናፊነትም ስለክብሩ መሞትን እንዲችል የአድዋ ጀግኖች በደምና በአጥንታቸው መሰረት ላይ ሀገር አፀኑ፡፡ ዛሬም እኛ በእነሱ ደም ላይ ታንፆ የፀናው መሰረታችንን በከፍታው ላይ ለማቆየት ይህንን እውነት ማመንና መቀበል ይኖርብናል፡፡ በእለት ተእለት እንቅስቃሴአችን በአካባቢያችን የሚገኙ በቅኝ ግዛት እና በባርነት ቀንበር ጥላ ስር ያለፉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ትኩረት ሰጥተን ለአፍታ እናስተውል እና አራሳችንን እንመርምር፡፡ያኔ አድዋ ምን ያህል ጥልቅ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ለተከፈለው መስዋዕትነት የሚመጥን ያህል ማድረግ ባንችል የሚገባውን ክብር እንስጣለን፡፡ያኔ አድዋ በምንም መስፈርት ፖለቲካ አለመሆኑን የሚገነዘብ ትውልድ ፤የሚረዳ ማህበረሰብ ማቆም እንችላለን፡፡

## ክብር ወድቀው ላቆሙን የአድዋ ሰማዕታት!!



## እንግዳ

ሰውን ለመርዳት ባላት እውቀትና ችሎታ ወደኋላ አትልም ይሏታል ፡፡ብዙ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የነቃ ተሳትፎም ታደርጋለች ፡፡በአካባቢው በሚከሰቱ አለመግባባቶች ውስጥ እሷን ለሽግልና የማይጠራት እንደሌለም ይነገራል፡፡የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲን በመስራችነት ከሚጠቀሱ ግንባር ቀደሞቹ ተርታም እሷ አለች፡የዛሬዋ የአድዋ ልዩ እትም እንግዳዬ በመሆን አብራን የምትቆየው ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው፡፡

ማሳሰቢያ ፡- ከኢንተርቪው በፊት ባለሙያ ፤ ባለሙያን አንቱ አይልም በማለቷ ምክንያት እንድጠራት በፈቀደችው መሰረት ቆይታ እንደምናደርግ ከወዲሁ ለማሳሰብ እውዳለሁ፡፡



**ዝክረ አድዋ ፡- በቅድሚያ ለዚህ ኢንተርቪው ፈቃደኛ በመሆንሽ በአንባቢዎቻችን ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው ፡-እኔም ይህ እድል ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁኝ፡፡

**ዝክረ አድዋ ፡- እስኪ ራስሽን በማስተዋወቅ ብንጀምር ?**

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው፡- ስሜ ይርጋለም በላቸው እባላለሁ ተወልጄ ያደግኩት አዲስ አበባ ጉለሌ አካባቢ ነው፡፡ከድምፃዊ መሐሙድ ጋር አብረን ነው ያደግነው፡፡ትምህርቴንም እዛው አዲስ አበባ ጉለሌ ውስጥ ስዊድሽ ሚሲዮን ትምህርት ቤት ነው የተማርኩት፡፡ከዛም ጎንደር ከተማ ነርሲንግ ተማርኩኝ፡፡ ትምህርቴን እንደጨረስኩኝ አዋላጅ በመሆን ጎርጎራ እንዳገለግል ተላኩኝ እዛ እያገለገልኩ ወደ ጎንደር ተዛወርኩኝ ከ6 ዓመታት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ጋንዲ ሆስፒታል ተዛውሬ ስራ ጀመርኩኝ፡፡ ጋንዲ እያገለገልኩ ትዳር ያዝኩኝ ልጆችን ወለድኩኝ፡፡ከዛም የትምህርት እድል በማግኘቴ በ1969 እኤአ አሜሪካን ሀገር መጣሁ፡፡

**ዝክረ አድዋ ፡- ህይወት እንዴት ተቀበለችሽ ?**

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው፡-፡- መጀመሪያ ስመጣ ህይወት በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ምክንያቱም ቤተሰቦቼን ትቼ ነው የመጣሁት ፡፡እና በተለይ ደግሞ የመጨረሻ ልጄ ገና ሁለት ወርም አልሞላውም ነበር ትቼው ስመጣ ፡፡ ትምህርት ቤት ለመግባት እድል ስለነበረኝ እናም ደግሞ እህቴም እዚህ ስለነበረች የመማር እድሉ እንዳያመልጠኝ በማድረግ እናቴ ነፍሷን ይማርና አሁን በህይወት የለችም፡፡ በእውነት በጣም በጣም እንድማር አበረታታችኝ ፡፡ ሂጂ ልጆቹን እኔ እጠብቃለሁ ፡፡ልጆችሽን ካንቺ ይበልጥ አሳድግልሻለሁ ሂጂ ስላለችኝ በሷ ብርታት ነው የመጣሁት፡፡በወቅቱ የኔም የመማር ፍላጎት ከፍተኛ ስለነበር መጣሁኝእና እዚህ ቫንደርቤልት ትምህርቴን ቀጠልኩኝ፡ ፡ እዚህ ከመጣሁ በኋላ በሁለተኛው ዓመት ወደ ኢትዮጵያ ለመጓዝ ስዘጋጅ ባለቤቴ ኤርላይንስ ስለሚሰራና ነፃ ትኬት ስለነበረው እሱ መጣ፡፡ ሲመጣ የጃንሆይ መውረጃ ግዜ አካባቢ ስለነበረ ነገሩ ሁሉ ኢትዮጵያ ውስጥ ጥሩ አልነበረም፡፡እና መጥቶ አይቶኝ ከሄደ በኋላ እዚህ ለመምጣት ሀሳቡን ለወጠ ፡ ፡ ልጆቹን ሰብስቦ መጣና እዚሁ ቀረን፡፡

**ዝክረ አድዋ ፡- ስንት ልጆች ነበሩሽ**

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው ፡- ልጆቼ ሁለት ወንድ አንድ ሴት በድምሩ ሶስት ናቸው፡፡ሁሉም የተወለዱት ኢትዮጵያ ነው፡፡

**ዝክረ አድዋ ፡- ከኢትዮጵያ ሲመጣ ትልቁ ፈተና የማህበራዊ ኑሮው የተለያየ መሆኑ እንደ አንድ ትልቅ ፈተና ይጠቀሳል እና ላንቺ እንዴት ነበር?**

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው ፡-አውነት ነው፡፡የሀገር ቤቱን ማህበራዊ ኑሮ ለምደህ እዚህ ያለውን ስታይ ይጨንቃል፡፡ እኛ እንደመጣን ብዙ ኢትዮጵያውያን አልነበሩም፡፡በጣም ጥቂቶች ነበርን፡፡እህቴም ተመልሳ ወደ ሀገር ቤት ሄደች፡፡እኔና ቤተሰቤ እና አንድ ሁለት ቤተሰቦች ብቻ ነበርን፡፡ሀገር ቤት የነበረውን ማኅበራዊ ኑሮ ለምደህ ከዛ ማኅበረሰብ ተነጥለህ በዚህ ሁኔታ ስትኖር ለመግለፅ የሚከብድ ፤ለመልመድም ፈታኝነው የሚሆነው፡፡አይለመድ የለ ለመድነው ፡፡ በሂደት ኢትዮጵያውያን አንድ ሁለት እያሉ መምጣት በመጀመራቸው ቁጥሩ እየጨመረ መጣ ፡፡ በጣም የሚገርመኝ ነገር ደግሞ በወቅቱ በኢትዮጵያ መንግስት ስኮላር ሺፕ እያገኙ ቫንደርቤልት ዩኒቨርስቲ የሚመጡ ብዙ ልጆች ነበሩ ፡፡የሚመጡት ሁሉ ኢኮኖሚክስ ነው የሚማሩት፡፡ሁሉም፡፡እና የሚመጡትን ሁላ እናውቃቸዋለን፡፡አናሳ ቁጥር ስለነበረን እንዲሁም አንዱ ለአንዱ ይነግረዋል ፤አንደኛው ሲሄድ ሌላው አለ፡፡እንደ ደረጃ ነው የምልህ መተካካቱ ፡፡አንዱ ሲሄድ ትምህርቱን ያልጨረሰ ሌላ ተማሪ አለ፡፡አንዱ ጨርሶ ተመልሶ ወደ ሀገር ቤት ሲመለስ ሌላ በኢትዮጵያ መንግስት ይላካል፡፡ እና በፊደት ነዋሪውም እየተጨመረ መጣ ፡፡ በዓል ሲሆን አንድ ቤት ተሰብስበን ነው የምናከብረው፡ ፡ እስላም አይል ፤የዘር ልዩነት፤የቋንቋ ልዩነት አናውቅም ሁላችንም ባንድ ላይ ተሰባስበን ነው በዓልን የምናከብረው፡፡እና ምንም እንኳን እንደ ሀገር ቤቱ ባይሆንም ከዛ ባልተናነሰ ሁኔታ ተሰባስበን በዓልን እናከብራለን፡፡በዛ መነሻት ነው እንግዲህ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ እናቋቁም

ብለን የጀመርነው:: እና እየቆየ ሲመጣ ግዜውም እየተቀየረ መጣ:: ስንጀምር በሀዘኑም በደስታውም አንተ ትብስ እኔ ተባብለን ጥሩ መንፈስ ኖረን ::የኤርትራ ነጻነት ተብሎ ሲታወጅ ነገሩ ሁሉ ተበላሸብን::(ረጅም ትንፋሽ በማቀርቀር)

ዝክረ አድዋ :- ምን ተፈጠረ ?

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው: እኛ ሁሉንም ነገር አላወቅነውም ነበር::ጓደኞቻችን ሁሉ አብረውን ይበሉ ይጠጡ የነበሩት ሁሉ ለካስ የራሳቸውን ግሩፕ አሰናድተው ተዘጋጅተው ነበር::እኛ ግን ምንም አናውቅም ይሄንን ::ማህበር እናቋቁም አንድ አይነት ማህበር ይኑረን እና ስም እናውጣ ተባለና አንድ ግዜ ብዙ ስለሆንን በቃ ማህበር ይኑረን ስም እናውጣለት ተባለ::የዛን ግዜ እዛ ላይ ጠብ መጣ ::ኢትዮጵያ የሚባል ስም እንዳይኖር አሉ::እንዴ ከየት መጣን ? የሁላችንም ፓስፖርት እኮ ኢትዮጵያ ነው የሚለው እንዴት ይሆናል? ሲባል ብዙ ጭቅጭቅ መጣ::ለማንኛውም ስም ይውጣ ሲባል የቀይ ባህር ጮራ፤ያባይ ፏፏቴ ... ሲሉ ባለቤቴ በጣም ተናዶ እኛ እኮ የኳስ ቡድን አይደለም የምናቋቁመው የኢትዮጵያ ማህበር ነው የምናቋቁመው አለ(የአግራሞት ሳቅ) :: አይ አይሆንም አሉ::እንግዲያው ነገሩ በይደር ይያዝ እና ይጠና ተብሎ 5 ሰዎች እንዲያጠኑ ተመረጡ::ያጠኑት ሰዎች መልስ ሊሰጡን ሁላችንም ተሰብስበን ሳለ ይቅርታ አድርጉልን አምስታችንም ስላልተስማማን ምንም አይነት ነገር ማድረግ አንችልም አሉ ::ከማህከላቸው አንዱ ተነስቶ ‹‹እኔ በጣም ነው የምወዳችሁ ጓደኞቼ ናችሁ ያለኝ አቋም ከናንተ ልዩ ስለሆነ እንደውም ከናንተ ጋር መቀጠል አልፈልግም›› ብሎ ተነስቶ ወጣ::ሌላኛውም ሳይናገር ተነስቶ ወጣ::ስለዚህ ፈረሰ:: ከዛ በኋላ ያመነበት ብቻ የኢትዮጵያ ማህበር ብሎ ኢማና/ኢካን/ን መሰረተ::ከዛን ግዜ ጀምሮ እየበዛ የሰውም ቁጥር እየጨመረ ልጅም እየተወለደ ሰርግም እያደረግን የሞተም እየቀበርን የሀገር ቤቱን ባህል ሳንለቅ ይኸው እስካሁን አለን::

ዝክረ አድዋ:- እንደ ኢትዮጵያዊ ኢካንን ስታቋቁሙ ህጋዊ ማህበርነቱን ለማስጠት የገጠማችሁ ፈተና ወይም በጎ ጎን ምን ነበር?

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው:- እንደ እውነቱ ምንም ፈታኝ ሁኔታ አልገጠመንም ያው አንፈልግም ብለው ከተለዩን ወዳጆቻችን በቀር ::ይልቁንም ባህላችንን እንድናስተዋውቅ ግፊት ያደርጉብን ነበር የአካባቢው አስተዳደር ሰዎች :: ኢካንም ሳይመሰረት ዩኒቨርስቲም እያለን የባህል ልብሳችንን ለብሰን ሀገራችንን እናስተዋውቅ ነበር::



እኛም ይህን እድል ተጠቅመን የባህል ልብሳችንን ለብሰን ኢትዮጵያን ይገልጻታል የምንለውን ሁሉ አቅም በፈቀደ እናስተዋውቅ ነበር

::በፈቃድ ረገድም ችግር አልገጠመንም እንደውም በአመቱ ነው ህጋዊ ሰውነት ሰርተፍኬቱ የተሰጠን::

ዝክረ አድዋ :- አሁን ያለውንና የድሮውን እናወዳድር ብንል እንዴት ይገለፃል?

ሲስተር:- እህህህ (ረጅም ትንፋሽ) ድሮ የነበረው ብዙው ነገር የቤተሰብ አይነት ነው:: እንደምሳሌ ብጠቅስልህ በእርግጥ በኢትዮጵያ የዚህን ያህል አይከበርም ክሪስ ማስ እዚህ ስናከብር ጊፍት ገዝተን እያንዳንዳችን እንለዋበጣለን::አንዱ ለሁሉም የመስጠት ልምዱ ነበረን::ይህ የሚያሳየው ምን ያህል መቀራረባችንን ነው::በእርግጥ ትንሽ ስለነበርን ነው::ሰዉ እየበዛ መንግስትም እየተለዋወጠ ሲሄድ የፖለቲካው ሁደትም እየተለዋወጠ መጣ::እኔ ለራሴ በጣም ነው ሾክ ያደረገኝ:: ምክንያቱም ከኢትዮጵያ ስወጣ ይህንን ሁሉ ነገር አላውቅም::ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ነች :: ሰው ሁሉ አንድ ነው የሚለውን የሙያዬን ስነምግባር ነው የማውቀው::ተወልጄ ያደግኩት መሀል አዲስ አበባ ላይ ቢሆንም ጉለሌ የሚታወቀው ብዙሀኑ የሚነጋገረው በኦሮምኛ ነው:: ጎረቤቶቻችን ግቢያችን ትልቅ ስለነበር ብዙ የሚከራዩ ቤቶች ነበሩን:: እነዛ ቤቶች ውስጥ አረቡች ተከራይተው ሱቅ ይሰሩ ነበር:: በሀገራችነር የሚነገሩ ቋንቋዎች ባለቤቶች ሁሉም አይነት ቋንቋ ተናጋሪ ነበር እዛ ግቢ የነበረው::ሁሉም ቤት እንገባለን እንወጣለን::ከሁሉም ጋር ነው ያደግነው::ችግሩ የመጣው እዚህ ስንመጣ ነው::እንዲህም አለ እንዴ እያልኩ ልክ እንደ ውጪ ሀገር ሰው ነበር ራሴን እቆጥረው የነበረው::መጀመሪያዎቹ ላይ ስንሰማው ያስደነግጥ ነበር::በኋላ ላይ ነው የመጣው እንጂ በፊት እንዲህ አይነት ነገር አልነበረም ::በጣም የማዝነው እኔ ልጆቼ አድገዋል ብዙ ነገር ያውቃሉ ::ግን የልጅ ሎጆቼን ምን ብዬ እንደምነግራቸው አላውቅም ::አንዳንድ ግዜ ሶሻል ሚዲያ ላይ አንዳንድ ነገር ሲመለከቱ ይጠይቁኛል እንጂ ማወቅም አይፈልጉም::አንዳንዴ እናንተ ኢትዮጵያዊያኖች ደግሞ ይላሉ የኔ ልጆች የሌሎቹን አላውቀም :: ምን አልባት ተመሳሳይ ነገር ይሉ ይሆናል::እና ያሳዝናል ::

ዝክረ አድዋ:- እና ሁሉም ሲቀየር ያልተቀየረው ባህላችን ብቻ ነው ለማለት ያስደፍር ይሆን?

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው :- የትኛው ያልተቀየረው ባህል

ዝክረ አድዋ :- አመጋገባችን::ሀበሻ አንዱ የሚታወቅበት መለያው የባህሉ መገለጫ እንበለው እንጀራ ነው ::በወቅቱ እንጀራ ከየት ነበር የምታመጡት?





ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው :- እንጀራ የሚባል ነገር የለም ::ፉርኖ ዱቄት ተበጥብብጦ ዝም ብሎ እንደ ፓን ኬክ አይነት አይን አወጣ አላወጣ ማስፋት ነው :: ያኔም ቢሆን እንጀራ በደንብ የሚታወቀው ዋሽግተን ዲሲ እና አካባቢው ብቻ ነበር :: እኛ ከምንኖርበት አካባቢ ርቀት የተነሳ ባላገሮች ነበር የሚሉን :: እና እንጀራ እንዴት እንደሚጋገር ሬስፒ አውጥተዋል::በዚህ ሀገር ሜተድ ሽሮ እንዴት እንደሚሰራ::በርበሬ እንዴት ሊዘጋጅ እንደሚችል ያዘጋጁ ስለነበር ለዛ ብለን ካሌንደሩን እናስገዛለን::እና በሱ እያየን እንጀራ ስንጋግር ከስኳር ነፃ የሆነ ኮካ ፤ጋዝ ያለው ሶዳ አይን እንዲያወጣ ጨምሩበት እየተባልን እሞክራለን::እንደ እውነቱ ከሆነ እንጀራ ብዙ ታሪክ ያለው ነው::አሁን ያለውን አንጀራ ከዛኛው ጋር ስታወዳድረው የሰማይና የምድር ያህል ርቀት ነው ያለው:: ዶሮ ወጥ እንኳን በደንብ አድርገን ሰርተን እንጀራው በምንፈልገው ሁኔታ ስለማይመጣልን በሩዝ ቀቅለን በሩዝ ላይ አፍስሰን ነበር የምነበላው::እንጀራንማ ያኔ ማን አግኝቶት:

## “ዶሮ ወጥ እንኳን በደንብ አድርገን ሰርተን እንጀራው በምንፈልገው ሁኔታ ስለማይመጣልን በሩዝ ቀቅለን በሩዝ ላይ አፍስሰን ነበር የምነበላው::እንጀራንማ ያኔ ማን አግኝቶት:”

ዝክረ አድዋ :- ኢትዮጵያውያን ለባህላቸው ቀናኢ ናቸው ይሄ ከምን የመጣ ነው?

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው:- የአድዋ ድል ውጤት ስለሆነ ነዋ::

ዝክረ አድዋ :-አልገባኝም ?

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው:- አየህ የአድዋ ጦርነትን ምን አልባት በዘመኑ የነበሩ አባት አርበኞች በድል ባይወጡት ኖሮ ምን አልባትም አሁን ላይ ባህላችን እንዲህ እንደሆነ ላይቀጥል ይችል ነበር::ምክንያቱም ወራሪዎች በውድም ይሁን በግድ የራሳቸውን ባህል እንድትከተል ነው የሚያስገድዱህ::ስለዚህ ባህል ክብር የምትላቸው ነገሮች ቅንጦት ሊሆን ይችል እንደነበረ ነው የሚሰማኝ::

ዝክረ አድዋ :- በእርግጥ አሁን ላይ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ አድዋን የሚረዳ ትውልድ ፈጥረናል ማለት እንችላለን ?

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው:- አይመስለኝም ምን አልባት ይህ ነገር የሚፈጠረው በዚህ ትውልድ ይሆናል ብዬ አላስብም::ልጆቻችንን እና የልጅ ሎጆቻችን ይረዱት ይሆናል የሚል እምነት አለኝ:: ምክንያቱም ሲርየስ አድርገው ብዙውን ነገር አያዩትም::እኛ ከስር መሰረቱን ሳናውቅ ዝም ብለን ስላደግን ነው የችግሩ ባለቤቶች የሆነውና እኛ ላይ መንጸባረቅ የሚታየው ::ለምሳሌ እዚህ ሀገር የነጮችንና የጥቁሮችን የአናኗር ሁኔታ ብትመለከተው ለልጆቻቸው ስለደረሰባቸው በደል ስለተፈፀመባቸው ግፍ እየተረኩላቸው እና እየነገሯቸው ነው ልጆቹ እያደጉ ያሉት:: ምክንያቱም የልጆቹ ወላጆች የችግሩ ገፈት ቀማሾች ሆነው ስለምታገኛቸው ነው:: በዓይናችን ያየነውም ብዙ ነው::እኛ ጋር ግን ስትመጣ የኛ እድገት ከላይ የጠቀስኩልህ አይነት ነው:: ከሁሉም ጋር ተግባብተንና ተጋብተን እንጂ እንደሚተረከው አይነት አይደለም::ሆኖም የተተረከውን ግራና ቀኝ ሳናይ አላምጠን ስለዋጥነው ችግሩ በኛ ላይ መንፀባረቅና መታየት ጀመረና ሁሉንም ነገር አበላሸው ::ቀጣዩ ትውልድ ራሱን በትምህርት እያነፀ ሲሄድና መጠየቅ ሲጀምር መንስኤና ምክንያቱ ላይ ስለሚደርስ አሁን እየተፈጠሩ ያሉት ችግሮችን የመቅረፍ እድሉ ይኖረዋል የሚል ተስፋ ነው ያለኝ::ልጆቹ አብረው እየተማሩ እና እያደጉ ነው ::በእውቀት ረገድ አይበላለጡም ስለዚህ ችግሮችን ለመቅረፍ ይከብዳቸዋል ብዬ አልገምትም::እና በቀጣዩ ትውልድ ተስፋ አለኝ::

ዝክረ አድዋ :- ቀጣዩ ትውልድ ከሚያድግበት ሀገር አንጻር ሀገር ቤት ተወልዶ እንደሚመጣው የስነልቦና ከፍታውን ጠብቆ ይሄዳል ወይ ከዚህ ሀገርስ የሚወርሰው ነገር አይኖርም ብለሽ ታምኛለሽ?

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው:- ልጆችህ ላይ መስራት ካልቻልክ::ባህልህን ታሪክህን እያስረዳህ ማሳደግ ከተሳነህ የዚህን ሀገርን ስነ ልቦና እንደማይወርሱ ምንም መተተማመኛ ማቅረብ አይቻልም::በቀለም ሆነ በቋንቋ ልዩነት የሚፈጠር የስነልቦና መወራረስ ፍርሀትና ስጋት ብሎም ጥላቻን ነው የሚያመነጨው::እንደዛ ሲሆን ደግሞ በራስ የመተማመን አቅምን ያዳክምና እዚህ ሀገር ያለው አይነት የጥቁሮችና የነጮች የበላይነት እና የበታችነት አይነት ስሜት የመስማት እድልን ይፈጥራል::ይህ እንዳይሆን ኢትዮጵያዊነት ማለት የላቀ ስነልቦና ያለው::ያልተበረዘ የራሱ ባህልና ወግ ቋንቋ እና ፊደላትን ቀርፆ ለአለም ያበረከተ:: እንደሆነ እየነገሩና የበለጠ ስለራሳቸው ታሪክ እንዲያውቁ እና እንዲያነቡ እንዲሁም ያልገባቸውን እንዲጠይቁ በማበረታታት ማሳደግ ያስፈልጋል::

ዝክረ አድዋ :- ስለ አድዋ ድል ምን ማለት ይቻለናል?

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው:- እኔ ምን ለማለት እንደምችል አላውቅም::የአድዋ ዘማቾች ምን ያህል ባለምጡቅ አዕምሮ ባለቤት እንደሆኑ ነው የሚሰማኝ::በፊት ላይ ስለ አድዋ የነበረኝ ግንዛቤ ይህን ያህል ነው ለማለት እቸገራለሁ::ከሀገር ቤት ከወጣሁም እረጅም ዘመኔ ስለሆነ ትኩረት ሰጥቼው አላውቅም ነበር::አሁን አሁን ብዙ መዛግብትን ሳገላብጥ በወቅቱ ያካሄዱትን ጦርነት እንዴት በጥበብ ልቀው ማሸነፍ እንደቻሉ ቀመራቸውን ስልትና ብልሀታቸውን ሳነብ የነበራቸውን የአዕምሮ ምጥቀት ነው ያሳየኝ::በተለይ ጠላትን ድል ለመንሳት የሄዱበትን ርቀት ፍልስፍና አልለውም ስልጣኔ ሳይ በእርግጥም

ከኛ የተሸሉ እንደነበር ነው ያለኝ መረዳት ::ይህንን ሁሉ ያደረጉትስ ለማን ነው ? ብዬ ራሴን ጠይቄ ያገኘሁት መልስ ለኔ ነው!::እኔ እኔን እንድሆን ያስደረገኝ ይሄ ታሪክ ነው:: እና ይሄንን ታሪክ ሳይዛነፍ ልጆቻችን ከስሩ እንዲማሩ ወላጅ አጥብቆ ልጆቹ ላይ መስራት ይኖርበታል::ዛሬ እንደ ቀላል የምናየው ነገ ላይ እንዲህ ላይሆን ይችላል::ከጥያቄህ እንዳያስወጣኝ እንጂ ባለፈው የአሜሪካ መንግስት በተመሳሳይ ፆታ ዙሪያ ትምህርት መሰጠት አለበት ሲባል ያልተደናገጠ? ሀገር ቤት ኢትዮጵያ ልኬ ከዚህ ወጪያቸውን እየላኩ እዛ ላስተምር ያላለ ማነው ? ለምንስ ልጁን እዛ ይልካል ልጆቹ ጥሩ እንዲሆኑለት አይደለም ስለዚህ እዚህ ያላስተማራቸውን እዛ ሄደው ምንድነው የሚሆኑት እና የሚፈጥሩት ::ስለዚህ እያንዳንዱ ወላጅ ቆም ብሎ ማሰብ እና ራሱን መጤቅ ልጆቹንም ማስተማር ይኖርበታል::

በቁ::የኛ ስነ ልቦና የሚቀዳው ከዛ ስለሆነ እንጂ የምንንቀው የሰው ልጅ ኖሮ አይደለም::

ዝክረ አድዋ :- በአንቺ ዘንድ አድዋ እንዴት ይገለፃል ?

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው :- በኔ በኩል



ማወቅ ይይቃል ::ከዛም ያወቁትን በንባብ ያዳበሩትን ልጆቹ በሚገባቸው ቋንቋና ሁኔታ ቀስ እያሉ እንዲገባቸው ማድረግ ያስፈልጋል:: አሁን ላይ ልጆቻችን እቤት ውስጥ በምናውራው ቋንቋ ካልሆነ በቀር ህይወታቸው ሁሉ የዚህን ሀገር ባህልና ወግን ልምምድ እያደረጉ የሚያድጉ ሆነዋል::ከቤት ውጪ የሚያገኙዋቸው መምህራኖች፤ጓደኞቻቸው ባጠቃላይ በዙሪያቸው ረጅሙን ሰዓት የሚያሳልፉት የዚህ ሀገር ሰዎችን ነው::ክትትልና ቁጥጥር አድርገን ይህንን ለመለወጥ ካልቻልን በኋላ የሚቸግረን ይመስለኛል::ልጆችን እውቀትን የሚይዙትም ክትትል የሚሹትም በአፍላ እድሜአቸው ነው::እና ለዚህ ቤተሰብ ታላቅ ሀላፊነት አለበት:: ምን አልባት በእኛ ግዜ ከተሳካ ደግሞ የኢካን እቅድ ተሳክቶ የኮሚዩኒቲው ማዕከል የሚሰራ ከሆነ ለብዙ እናቶች የስራ እድል ለመፍጠርና ልጆቻችን ከዴይ ኬር ጀምሮ አፍተር ስኩልን ጨምሮ ልጆችን በመንከባከብ ረገድ ለብዙ ኢትዮጵያውያን እናቶች የሚተው ስለሆነ የተሻለ እድል ስለሚፈጥር ቤተሰብ ቢያንስ አሁን ያለበትን ውጥረት ሊያቀልለት ልጆችም በሀገራቸው ሰው ስለሚጠበቁ ፤ኢትዮጵያውያን እናቶችም እንደ ስራ ሳይሆን እንደ ልጅ ስለሚቆጥሯቸው፡ እንክብካቤ ስለሚያደርጉላቸው ልዩነቱ የመጥበብ እድሉ ይኖራል የሚል እምነት አለኝ::

ዝክረ አድዋ :- ኢትዮጵያውያን ሰው ይንቃሉ ይባላል ይህንን እንዴት ታይዋለሽ?

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው :- ሰው አንንቅም::ግን ጥዩፎች ነን::ነውር ብሎ ባህላችን ያስቀመጠውን ነገር አንደፍርም:: በክርስቲያኑም መፅሀፍ ቅዱስን በሙስሊሙም ቅዱስ ቁርዓን ያስቀመጧቸውን መጠሪያዎች በአግባቡ እየተጠቀምን ያደግን ህዝቦች ነን:: ሌላው እያንዳንዱ ማህበተሰብ ራሱን የቻለ የራሱ ባህል አለው::እኛም የማንደራደርባቸው የራሳችን የሆኑ ባህሎች አሉን:: አንዳንዴ ሁሉም አይነገርም ይባላል::እውነት ነው:: በልባችን ፅፈን ያስቀመጥናቸው ግን ደግሞ የማንናገራቸው ነገሮች አሉ::እነዛ ለሌላው እንደ አላዋቂ ወይም ዘመኑን እንደማይመጥን አድርጎ የሚያስቆጥር ተደርጎ ሊታይ ይችላል::ነገር ግን ኢትዮጵያዊ ከኢትዮጵያዊ ጋር በአርምሞ ይግባባበታል::አንዳንዴ እንዲህ አይነት ትችቶች የሚፈጠሩት ኢትዮጵያውያንን ካለማወቅም ጭምር ነው::እኛ ያላከበርናቸው ግን ለዓለም ያበረከትናቸው አያሌ ነገሮች አሉ::ለራሳችን ክብር መስጠት ስንጀምር እነዚህን ነገሮች ማክበር እንጀምራለን::የአድዋ ትሩፋት አንዱ ይህ ነው::እኛ ከማንም የወሰድነው የለም::እምነትና ባህላችንን ሊነጥቀን የመጣን ጠላት ድል ነስተን ወደመጣበት መለስነው::የኛ ድል ለሌሎች አርአያ ሆነ::ሳንቀበል ለሌሎች ፈለግ እንዲሆን ሰጠን::ከኛ ባዩት በጭቆና ስር የነበሩ ሁሉ መንገዳችንን ተከትለው ለድል

አድዋን እያሰብኩ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብዬ የምኮራበት ልቤ የሚሞቅበት የአድዋው ድል ታሪክ ነው:: በአይነ ህሊናዬ ወደኋላ ሄጄ የተደረገውን እያሰላሰልኩ እያወጣሁ እያወረድኩ እቃኘዋለሁ::በዘመኑ ባልኖርም ታሪኩ በማይደበዝዝ ቀለም ተፅፎ ተቀምጦልናል በየ ዓመቱ ለኔ አዲስ ነው::አይረሳም::አለሙ ክፉ ነው በቆዳ ቀለም ነጭ እና ጥቁር እያለ ጎራ ለይቶ አስቀምጦናል::እናም እኔም አመጣጤ ከጥቁሮች ምድር ቢሆንም ልቤ ግን ብርሀን አለው::ብርሀኑ የሚመጣው ደግሞ ከአድዋ ነው::በታሪክ በቅኝ ግዛት ያልተገዛች ጠላትን ድል አድርጋ የመለሰች ሀገር ማናት ተብሎ ሲጠቀስ የምትገኘው ሀገር በዓለማችን ብቸኛዋ ኢትዮጵያ ብቻ ናት::ይህ ደግሞ በኔ ዘንድ ከፍ ያለ ስሜት ነው የሚፈጥረው:: አሁን ላይ ቁጭ ብዬ ያለንበትን ሳይ በስልጣኔ ሳይሆን በታሪክ ነው ከፍታዬን የማየው::በስልጣኔ ብዙ ይቀረናል::በእርግጥ ስልጣኔን ግዜ የሚያመጣው እንደሆነ አምናለሁ::ታሪክህ ግን ታሪክህ ነው::እንዳለ ነው ይህን ስል በታላቅ ኩራት ነው::

ዝክረ አድዋ :- አንቺ የሚሰማሽን ኩራት እንዴት ወደ ልጆቻችን ማስተላለፍ ይቻላል?

ሲስተር:- መጀመሪያ የተደረገልንን

ዝክረ አድዋ :- በኢካን ዙሪያ ወደፊት በስፋት ስለምንጨዋወት ለዛሬው ማስተላለፍ ወይም ማለት የምትፈልጊው ነገር ካለ?

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው :- እኔ ምንም የምለው ነገር የለም ::እናንብብ እንወቅ:: ያወቅነውን ሼር እናድርግ ነው ::

ዝክረ አድዋ :-ስለነበረን ቆይታ ከልቤ አመሰግናለሁ !

ሲስተር ይርጋዓለም በላቸው :-አመሰግናለሁ::



# የአንድ - አፈር - አፈሮች



ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም

ፍቅራችንን
ድንበር ወሰን ላይገድበው፡
ሁለት ክልል ላይመጥነው፤
መገዳደል ፍት’ ላይሆነው::
በሽንፈትህ እሠይ ላልል፤
በሽንፈቴ እፎይ ላትል፤
ከቂም በቀል ፍቅር ላይበቅል::
ልጅህ በእጄ ለምን ይሙት፤
ልጄስ በእጅህ ለምን ትሙት::
እኔና አንተ እኮ፤
የአንድ እናት ልጆች፤
ወንድማማቾች፤
ያንድ አፈር አፈሮች::
ርስት አፈሩማ
ይቅርም ከወደዚህ ይሂድም ወደዚያ፤
ያው ነው የኢትዮጵያ ያንድ አፈር መጠሪያ::
ወዲያ ካለው የቀድሞዋ ወዲህ ካለው የእስካሁኗ
ግዳይ ጥዬ በልጅህ ደም በጀግንነት ላልጠራ፤
ግዳይ ጥለህ በልጄ ደም ላትፎክር ላታቅራራ::
ወንድም ገድለው ላይፎከሩ፤
ጀብዱ ሰርተው ላይኩራሩ፤
ያዘን ሙሾ ሊዘምሩ::
እንደ ማተብ የእምነት ክር ፍቅር ድሩ ላይበጠስ፤
ባዘናችን ላትዘፍኑ በሞታችሁ ላንደንስ፤
ስሙር አይሁን ነጭ ሴራው ደስ አይበለው
የጠላት ነፍስ::
ልጅህ አይሙት በልጄ ጣ ት፤
ልጄም አይሙት በልጅህ ቀስት::
እኔና አንተ እኮ
ከዘመናት በፊት፤
በታሪክ በሃይማኖት፤
በባህል በትውፊት::
በደስታ በችግር
ስም የለሽ ስመ-ጥር፤
በጋሻና በጦር ጀብደኛ ባላገር፤
ያንድ አያቶች ዘር የሁለት አፈር ሠፈር::
ስም የለሽ በጥጋብ፤
ስመ-ጥር በረሃብ::
እያሉ ሲተቹህ እያሉ ሲተቹን፤
በሙጫ ስድብ አጣብቀውን::
ሲተቹን መተቸት ሲተቹህ መተቸት፤
እንዳለ ስናውቀው እንዳለ ስታውቁት::
ካንድ እናት ተወልደን በሁለት አባት አድገን፤
አንድ ውሃ ተራጭተን አንድ አፈር አቡክተን::
ቃታ ስንሳሳብ
እሺ ላይለው ልብህ ደስ ላይለው ልቤን፤

እኮ እንዴት እኔና አንተ ዛሬ እንዲህ እንጫከን ::
እኔና አንተ እኮ
ያንድ እናት ልጆች፤
ወንድምና እህቶች፤
ያንድ አፈር አፈሮች::
እናም ወንድም ስማኝ ልስማህ
ደስ አይበለው ነገር ሰሪ አንተን ከኔ ጸብ ሲያቃባ፤
እንዘምር ባንድ እንዝለል ወሰን አይኑር የደም ካባ::
በመሞትህ ደስ ላይለኝ ውስጥ ልቤ እዥ ሊያነባ፤
የናቱን ልጅ ልጅህ ገድሎ ላያሰማ ጉሮ ወሸባ፤
ፍቅር እንጂ ግድባችን ወሰን አይኑር የደም ካባ::
ይልቅስ ልንገርህ፤
ኩራቴ ኩራትህ፤
ታሪኬ ታሪክህ፤
የሚያመጻድቀኝ የሚያመጻድቅህ፤
የኔም ያባቴ ነው ያንተም የአባትህ::
ከቢዘን ባስቀድስ ከግሸን ብትሰልስ
በአክሱም ብትኮራ፤
ብሸልል በአስመራ::
ያንተ አባት አባቴ አባቴ አባትህ፤
የሚያመያጻድቀኝ የሚያጻድቀኝ ታሪኬ
ታሪክህ::
መሆኑን ስናውቀው መሆኑን ስታውቁት፤
በደምና ባጥንት በስጋ በጅማት በታሪክ
በትውፊት::
መንታ ናቸው ሲሉን፤
እኮ እንዴት እኔና አንተ ዛሬ እንዲህ እንጫከን::
በብቀላ ጸጸት በቀር ወንድም ጥሎ ላይፎክር፤
ጀግና ተብሎ ሜዳይ ላይኖር::
በናቴ ልጅ በመጨከን እሺ ላይለኝ የልቤ በር፤
ወንድ ልጄን ግዳይ ጥለህ ላይፈታ የደምህ ስር::
ካንድ ደብር አድገን በአንድ አስቀድሰን አንድ
ዳዊት ደግመን፤
ካንድ መስጊድ ኖረን ባንድ ሰላት አድገን አንድ
ቁርዓን ቀርተን፤
እኮ እንዴት እኔና አንተ ዛሬ እንዲህ እንጫከን::
ለጉዳትህ ተሰዉቼ ፤
ላንተ ክብር ብዙ ሞቼ::
ስላንተ ነጻነት ካገርህ ደሜ አለ፤
በናቅፋ ተራሮች እቅፍ የታዘለ::
መጎዳቴን እምቢ ብለህ፤
ስለ ክብሬ ተሰውተህ፤
የሰጠኸኝ ክቡር ደምህ::
ያንተም አጽም ዓድዋ አለ፤
ለጦቢያ ነጻነት ስለኔ የዋለ::
መንታ ናቸው ሲሉን፤

ፍቅር ናቸው ሲሉን፤
እያወቁት ልቦናችን፤
ሁለት ክልል ላይመጥነን፤
ድንበር ወሰን ላይገድበን፤
መገዳደል ፍት’ ላይሆነን::
በሽንፈትህ ስንዘምር “በለው” ያሉን ሊታዘቡን፤
ነጭ ሴራ ወጣው ሊሉን::
ስጋ ክንድህ ሲደማብህ ልቦናችን ሊያዝብን፤
ባለም ዜና ድላችንን ደም ጥማት ነው፤
ብለው ሊሉን::
ልጅህ በጄ ለምን ይሙት፤
ልጄስ በእጅህ ለምን ትሙት::
ስማኝ ወገን
ደስ አይበለው ነገር ሰሪ አንተን ከኔ ጸብ ሲያቃባ
ስሙር አይሁን ነጭ ሴራው
የሸረበው የሞት ደባ ፤
እንዘምር ባንድ እንዝለል ወሰን አይኑር የደም ካባ::
ርስት አፈሩማ
ይቅርም ከወደዚህ ይሂድም ወደዚያ፤
ያው ነው የኢትዮጵያ አንድ አፈር መጠሪያ ::
ወዲያ ካለው የቀድሞዋ ወዲህ ካለው
የእስካሁኗ
እናም በሞትህ ትሙት ፤
እናም በሞትህ ትሙት፤
እኔና አንተ አንሙት ::
እኔና አንተማ የአንድ እናት ልጆች
ወንድምና እህቶች
ያንድ አፈር አፈሮች ::



# አድዋና ኢትዮጵያዊነት ለጥቁር ህዝቦች!

ዶ/ር ጋሻውበዛ በቀለ (ፐ/ር)



ጀግኞች አባቶቻችን የዛሬ 129 ዓመት ከያሉበት ወደ አድዋ በመትመም ለኢትዮጵያውያን እና ለመላው የጥቁር ህዝቦች የነጻነት እና የአሸናፊነት ምልክት የሆነውን የአድዋን ድል ተጎናጽፈውለትውልድአስረክበውአልፈዋል።ምንምእንኳን ጦርነቱ የተጠናቀቀው እ,ኤ,አ, መጋቢት 1 ቀን 1896 ዓ,ም, (የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. ) አድዋ ላይ ቢሆንም የክተት አዋጅ ከታወጀበት ከመስከረም 17 ቀን 1888 ጀምሮ ጦርነቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ 5 ወራትን የፈጀ፣ ከ1,000 ኪሎ ሜትር በላይ የሚፈጅ እግር ጉዞን ያስተናገደ፣ ከአድዋ በተጨማሪ በአምባላጌ እና በመቀሌ በተደረጉ ዉጊያዎች ኢትዮጵያዉያን ድልን የተቀናጁበት እንዲሁም የኢትዮጵያ ጦር የአመራር ብስለት፣ የወታደራዊ፣ የመረጃ እና የዲፕሎማሲ ብልጫ የታየበት ታሪካዊ ጦርነት ነው። ታዲያ ይህን ያአድዋ የድል በዓል በየዓመቱ ስንዘክር አባቶቻችን ልዩነቶቻቸውን ሁሉ በመተው በአንድነት የከፈሉትን ታላቅ መስዋዕትነት በአንክሮ መመልከት፣ የአድዋ ድል ለኢትዮጵያውያን እና ለመላው ጥቁሮች ያለውን ዓለም አቀፋዊ ፋይዳ ማገናዘብ እና የዛሬዋን ኢትዮጵያን በአንክሮ በመመልከት አርበኞች አባቶቻችችንን የሰጡንን አደራ ጠብቀናል ወይስ በልተናል በማለት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እራሱን ሊጠይቅ ይገባል። ምንም እንኳን በእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል እንደሚባለው ምናልባት የዚህ ድል ጠቀሜታ ለአንዳንድ ኢትዮጵያውያን ቢሰወርባቸውም ይህ ጽሁፍ የአድዋ ድል ለጥቁር ህዝቦች የነበረውን ፋይዳ በአጭሩ ይዳስሳል።

ምንም እንኳን የአድዋ ድል ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ይበልጥ ያስተዋወቀ እና ለተጨቆኑ ህዝቦችም የነጻነት እና ሉዓላዊነት ትግል ፋና ወጊ ቢሆንም ከአድዋ በፊት ኢትዮጵያዊነት የጥቁር ህዝቦች ከተጫነባቸው የባርነት እና የጭቆና ቀንበር ለመውጣት በሚያደርጉት ትግል ውስጥ ትልቅ ቦታ የተሰጠው ርዕዮተ ዓለም ነበር። ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያዊነት በሰሜን አሜሪካ፣ በካሪቢያን፣ በአውሮፓ እና በአፍሪካ አህጉር ለሚገኙ የአፍሪካ ህዝቦች ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና መንፈሳዊ ተስፋቸውን መግለጫ ነበር። ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚለው ትንቢታዊ ቃል ጥቁሮች ከባርነት እና ጭቆና ነጻ እንደሚወጡ አመላካች ተደርጎ ስለሚታይ እና ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በታሪክ ማህደሮች ላይ በተደጋጋሚ የተጠቀሰች በመሆኗ በተለይ በጥቁር ህዝቦች ዘንድ ትልቅ ቦታ እና ክብር እንድታገኝ አድርጓታል። በተለምዶ ኢትዮጵያ እንደ "አፍሪካዊት ጽዮን" የምትታይ ስትሆን የጥቁር ህዝቦች በቅኝ ግዛት፣ ፍትህ በማጣት፣ በባርነት፣ በዘረኝነት በሚንገላቱበት ዘመን ፓን አፍሪካኒዝም የሚባለው የአፍሪካዉያን የጋራ ንቅናቄ ከመጀመሩ በፊት ኢትዮጵያዊነት የጋራ አፍሪካዊ ማንነት እና በቅኝ ገዥዎች ላይ ለሚደረግ ማንኛውም ትግል የነጻነት እና የአንድነት ትግል መጥሪያ ደወል ሆኖ አገልግሏል።

በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ጥቁሮች መጽሐፍ ቅዱስን በማጣቀስ ኢትዮጵያን የተስፋይቱ ምድር አድርገው ይመለከቷት ስለነበር ቤተ እምነቶታቸውን ኢትዮጵያ፣ አቢሲኒያ ወይም አፍሪካ በማለት ሰይመዋል።

> "83 ዓም ጃማይካ ውስጥ ጆርጅ ሊሌ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ሲመሰርት የኢትዮጵያ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ብሎ በመሰየም የማርከስ ጋርቬይ እና የራስ ተፈሪያን እንቅስቃሴ የትውልድ ቦታ በሆነችው ጃማይካ ውስጥ ኢትዮጵያዊነትን አስተዋውቋል።"

በአሜሪካ ቤተክርስቲያን ውስጥ በዘር መድልዎ ምክንያት ነጭ እና ጥቁር አንድ ላይ መቀመጥ በማይፈቀድበት ዘመን ጥቁር አሜሪካውያን ነጻ የሆነ ቤተክርስቲያን እ.ኤ.አ. በ1808 ሲያቋቁሙ ቤተክርስቲያናቸውን በኢትዮጵያ የቀድሞ ስም አቢሲኒያ Abyssinian Baptist Church በማለት የሰየሙ ሲሆን በደቡብ አፍሪካም እ.ኤ.አ. በ1892 ዓ.ም. the Ethiopian Church of Pretoria የሚባል ቤተ እምነት አቋቁመዋል። ጥቁሩ ሰባኪ ሮበርት አሌክሳንደር ያንግ በ1829 ዓም በኒውዮርክ ባሰራጨው የኢትዮጵያ ማኒፌስቶ (The Ethiopian Manifesto, Issued in Defence of the Blackman's Rights, in the scale of Universal Freedom) በተሰኘው በራሪ ወረቀት ጥቁሮች ከባርነት ወጥተው በነጻነት መኖር እንዳለባቸው በማወጅ በመጽሐፍ ቅዱስ መኳንንት ከግብጽ ይመጣሉ፣ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች በሚል የተገለጸችውን ኢትዮጵያ መላ አፍሪካውያንን የምትወክል የጥቁሮች የተስፋ ምድር መሆኗን አመላክቷል። በደቡብ አፍሪካ ነጻ ቤተክርስቲያን በ1892 ያቋቋሙት የሃይማኖት አባቶችም በ1896 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ማኒፌስቶ የሚል ጽሁፍ በማዘጋጀት በዓለም የተሰራጩት አፍሪካውያን ተባብረው አንድ ቤተክርስቲያን እንዲመሰርቱ እና አፍሪካ ለአፍሪካውያን መሆን እንዳለባት አዉጀዋል። በ1896 ዓም የኢትዮጵያ መንግሥት ጣልያንን በአድዋ ጦርነት ድል ካደረገ በኋላ የጥቁር ህዝቦች ለኢትዮጵያ የሚሰጡት ቦታ ከፍ ያለ ሲሆን ኢትዮጵያዊነት የነጻነት እና የጀግንነት ምልክት እንዲሁም አድዋ ቅኝ ገዥዎችን ድንጋጤ ውስጥ የከተተ የጥቁር ህዝቦች የተቃዉሞ አርማ እና የትግል የማንቂያ ደወል እንዲሆን አድርጓል። በአድዋ ጦርነት ወቅት እና ጦርነቱ ባለቀ ማግስት አብዛኞዎቹ የውጭ እና የአፍሪካ ጋዜጦች በነጮች ቁጥጥር ስር ስለነበሩ የሚዘግቡት ዘገባ ለጣሊያን ያደላ ቢሆንም ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ ግን ሳይወዱ በግድ የጣሊያንን ሽንፈት ለመዘገብ ተገደዋል። በዚህም ምክንያት የአጼ ምኒልክ እና እቴጌ ጣይቱ እውቅና በውጭው ዓለም የጨመረ ሲሆን የአሜሪካ ጋዜጦች አጼ ምኒልክን እንደ ራሽያው ኒኮላስ 2ተኛ ነጭ አድርገው በመሳል አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያዉያን ነጮች (Caucasian race) ናቸው በማለት የዘረኝነትን ሃሳብ ቀጥለውበት ታይተዋል። ሆኖም ግን እንደ ዱቦይስ፣ ማርከስ ጋርቬይ፣ አይዳ ቢ ዌልስ፣ ቤኒቶ ሲልቪያን፣ ቡከር ዋሽንግተን እና ዮሴፍ ቪታልየንን የመሳሰሉ የጥቁር መብት ተሟጋቾች፣ መሪዎች፣ እና ምሁራን የአድዋ ድልን ከሰሙ በኋላ የመላው ጥቁር ህዝብ የነጻነት ትግል ይበልጥ እንዲቀጣጠል አድርገዋል። አጼ ሚኒልክ ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ ምሁራን እና የንግድ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ግብዣ በማቅረባቸው ንጉሡ የተቀዳጁትን ድል ፓሪስ ሆኖ የሰማው ሔይቲ የተወለደው ቤኒቶ ሲልቪያን የጥቁሮችን መብት ስለማስጠበቅ ይጽፈው የነበረውን ጋዜጣ ጥሎ አጼ ምኒልክን ለማግኘት ወደ ኢትዮጵያ ተጉዟል። ቤኒቶ ሲልቪያን ወደ ኢትዮጵያ የሄደው እ.ኤ.አ. በጥር 1897 ዓ.ም. ሲሆን በኢትዮጵያና ሔይቲ መካካል የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ከማድረግ ባሻገር 4 ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ አጼ ምኒልክ የጥቁርን ዘር አኗኗር ለማሻሻል የመሪነት ሚና እንዲጫወቱ በማግባባት እና በ1900 ዓ.ም. ለንደን በተካሄደው የፓንአፍሪካ ስበሰባ ላይ ኢትዮጵያን እና ሔይቲን በመወከል ተሳትፏል። በዚሁም ስብሰባ አጼ ምኒልክ የፓንአፍሪካ ማህበር የክብር አባል ሆነዋል። ዮሴፍ ቪታልየን የተባለ ሐኪምም ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ የምኒልክ የግል ሐኪም ሆኖ ማገልገሉ ብቻ ሳይሆን በሁለተኛው የአፍሪካውያን ጉባኤ ኢትዮጵያን ወክሏል። ቤኒቶ እና ዮሴፍ እንደ ቦብ ማርሊ ኢትዮጵያን እንደ አዲሲቷ ጽዮን አድርገው የሚያዩ የጥቁር መብት ታጋዮች ነበሩ። ከዚህ በተጨማሪ በ1903 1904 ዓም የኩባ-አሜሪካዊው ዊሊያም ኤች ኤሊስ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልማት እና ለጥቁር አሜሪካውያን ኢትዮጵያ ዉስጥ ዳግም የሚሰፍሩበትን እቅድ ይዞ ሁለት ጊዜ ኢትዮጵያን ጐብኝቷል። ከዚህ በተጨማሪ ታዋቂው ጥቁር አሜሪካዊው ምሁር ዱቦይስ ጀርመን በአንደኛው የዓለም ጦርነት ከተሸነፈች በኋላ በ1918 ዓም ፓሪስ በተካሄደው "የሰላም ስበሰባ" ላይ የጀርመን ቅኝ ግዛት የነበሩት የአፍሪካ ሃገራት በአንድነት ኢትዮጵያን ዩቶፒያ (Ethiopian Utopia) የሚባል ሃገር እንዲመሰርቱና እና ከአሜሪካ፣ ከኢትዮጵያ፣ ከላይቤሪያ እና ከሔይቲ የተውጣጡ ጥቁር መሪዎች እንዲያስተዳድሩት ሃሳብ (proposal) አቅርቦ ነበር። ታዋቂው የፓን አፍሪካኒስት መሪ ማርከስ ጋርቬይም ጥቁር ህዝቦችን ለማስተባበር እና ኑሯቸውን ለማሻሻል ባቋቋመው ማህበር Universal Negro Improvement Association (UNIA) ይዘመር የነበረው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ብሔራዊ መዝሙር ነበር። የህዝብ መዝሙሩ "ኢትዮጵያ ሆይ የአባቶቻችን ምድር፣ አማልክት ከአንቺ ጋር ለመሆን የወደዱባት መሬት..." በማለት ኢትዮጵያ አፍሪካዊ ማንነትን እንድትወክል በማድረግ በጥቁር ህዝቦች ውስጥ የአድዋ መንፈስ ትልቅ ስፍራ እንዲሰጠው አድርጓል። አጼ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉሥ ሲሆኑ ምንም እንኳን በአድዋ ጦርነት ላይ ባይሳተፉም የአድዋ አሻራ እና ኢትዮጵያዊነት ተከትሏቸዋል። በተለይም ራስ ተፈሪያኑ ኢትዮጵያን ቃል የተገባላት የተስፋይቱ ምድር ነች ብለው የሚያምኑ በመሆናቸው የአጼ ኃይለ ሥላሴ የንግሥና ሲመት ሲፈጸም እና የጥቁር ንጉሥ ዘውድ ሲቀዳጅ አምላክ በስጋ የተገለጠበት እለት አድርጎ በመቁጠር ንግሥናቸውን የነጻነት ቀን መቃረቡን የሚያሳይ ክስተት ነው በማለት ገልጸውታል። አጼ ኃይለ ሥላሴ በካሪቢያን ደሴት አገራት ታሪካዊ ጉብኝት በማድረግ፣ ኢትዮጵያ ዉስጥ 500 ጋሻ መሬት ጃማይካዉያን እንዲሰፍሩበት በመስጠት፣ ከጥቁር ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲቋቋም በማድረግ ኢትዮጵያዊነትን በጥቁሩ ዓለም ምናብ ውስጥ ከፍ ያለ ስፍራ እንዲኖረው አድርገዋል። የጣሊያን መንግሥት ከ40 ዓመት ዝግጅት በኋላ ኢትዮጵያን በድጋሚ የወረረ ጊዜም ጥቁር አሜሪካዉያን ወረራው በአፍሪካ የነጻነት፣ የሉዓላዊነት ምሳሌ በሆነችው ሀገር ላይ የተቃጣ ጥቃት በመሆኑ እና ትግሉ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የጥቁር ህዝብ ትግል በመሆኑ ጦርነቱን በመቃዎም ሰላማዊ ሰልፍ በመዉጣት እንዲሁም ከኢትዮጵያዉያን ጎን ተሰልፈው ከፋሽስቱ የጣሊያን መንግሥት ወታደሮች ጋር ለመፋለም ተመዝግበዋል። ጆን ሮቢንሰን እና ሁበርት ጁሊያን የተባሉ የአውሮፕላን አብራሪዎችም ኢትዮጵያ በወቅቱ የነበሯትን ሁለት አውሮፕላኖች ለማብረር ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ በፈቃደኝነት የሄዱ ሲሆን ከወረራውም በኋላ በበረራ አሰልጣኝነት አገልግለዋል። በጣሊያን የአምስት ዓመት ወረራ ወቅትም የአጼ ኃይለ ሥላሴ የግል ሐኪም በነበሩት ዶክተር መላኩ በያን እና በአፍሪካን አሜሪካውያን የተመሰረተው

... ወደ ገፅ 12 ዞሯል

# አድዋ፡ የማይናወጥ አለት



ያሬድ አማረ ውብነህ

የታላቁ የአድዋ ድል በዓል በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብቻ ሳሆን በባርነት ቀንበር ስር ለነበሩ ሁሉ ፋና ወጊ በመሆኑ በየዓመቱ የሚዘከር ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የጥቁር ህዝቦች የድል ብስራት ፋና ወጊ በዓል ነው፡፡ ሆኖም በእውቀት ማጣትም ይሁን ለራስ የሚሰጥ ክብር ማነስ በራሳችን ሰዎች የሚሰነዘረው መሰረት አልባ ተረክ የአድዋ ድል በዓል የሚገባውን ክብር እንዳያገኝ ለማድረግ የተሄደበት እርቀት አስተዛዛቢ ሆኖ እናገኘዋለን ፡፡ያም ሆኖ የአድዋ ድል ታሪክን ማንም ሊያጠፋው ወይም ሊፍቀው በማይችል በደም ቀለም የተፃፈ አኩሪ ገድል ነውና በዓለም ታሪክ ውስጥ ፀንቶ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተረክ ይኖራል ።

እኛም ባህር ማዶ ያለን የታሪኩ ባለቤቶች ነን የምንል ሁሉ 129ኛውን የአድዋ ድል በዓልን በታላቅ ክብርና የመንፈስ ልዕልና እናስበዋለን፡፡ የአድዋ ድልን ማክበር ክብርና ኩራቱ ለእኛ እንጂ ታሪኩን ለሰሩትና ላለፉት ምንም የሚጨምር ወይም የሚፈይድላቸው ነገር የለም፡፡እነሱ መሆን የነበረበትን፤ማድረግ በነበረባቸው አድርገው አልፈዋል፡፡ክብራቸውን ጠብቀው በደም በአጥንታቸው መሰረት ሀገር አቆይተው አልፈዋል፡፡ ይህም ታሪካቸው ለዘለዓለም ሲወሳና ሲወደስ ይኖራል፡፡

የአውሮፓ ሀገራት በጀርመን ስብሰባቸው አፍሪካን የመቀራመት የወጠኑት ህልምን ተግባራዊ ለማድረግ እስካፍንጫው የታጠቀ ዘመናዊ (በወቅቱ የነበረው የስልጣኔ ደረጃ) የጦር መሳርያና ፤ በጦርነት ስልጠና የተገራ ወታደር አሰልፈው በአፍሪካ ምድር በመሳሪያ አፈሙዝ ተመርተው በምድሪቱ ሞሉ ፡፡ ድንበር አስምረው ኬላ ከልለው አፍሪካንም ተቀራመቷት፡፡ በወቅቱ በነበራቸው ትእቢትና ንቀት ምኞታቸውን ሊፈፅሙ በሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል ጣሊያኖች ሰፈሩ ፡፡

በተፈጥሮ መሰረቶች ላይ የተንጠለጠለው የሰፊው ህዝብ የመኖር ህልውና ከዝናብ ጥገኝነት ያልተላቀቀ በመሆኑ የተነሳ ያንዣበበው የረሀብ ጥላ ሳይፈታ የቀኝ ገዢዎች ወረራ ሲታከልበት በወቅቱ ለነበሩት መሪ ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ምን ፈታኝ እንደነበር ለመናገርና አልያም ለማስረዳት በእሳቸው ጫማ ውስጥ መግባትን ይጠቃል ፡፡ በረሀብ እየተገረፈ ያለን ህዝብ ለጦርነት እንዴት ልትልከው ትችላለህ ? እንዴትስ በርትቶና ርሀቡን ተቋቁሞ የድሉ ባለቤት ሊሆን ይችላል ? ብለህ እምነት ትጥልበታለህ? የዚህ ሚስጥር ፍቺ እንዲገለፅልህ ሚኒሊክን ካልሆንክ በቀር የሚቻል አይመስለኝም፡፡

ሆኖም ተችሎ በዓለም አደባባይ ድሉ ታየ፡፡በክብሩ ከመጡበት ሀበሻ የሚሰስተው ነገር እንደሌለ በደሙ ቀለም በዓጥንቱ መሰረት ሀገሩን አፀና፡፡የጣልያን መሸነፍ ለአፍሪካውያን ጭቁን ህዝቦች ብቻ ሳይሆን በባርነት ቀንበር ስር ለሚገኙ በመላው ዓለም ላሉ የይቻላል መንፈስን አጎናፅፎ ለነፃነት ትግል እንዲደረግ ብስራትን ሆነ። በጨለማ ውስጥ ለነበሩ ሁሉ መንገድ አቅኚ የብርሀን ፈንጣቂ ኮከብ ሆኖ ታያቸው፡፡የአድዋው ድል፡፡

ቅድመ አያቶቻችን ትክ አልባ ህይወታቸውን ገብረው ሊያደርጉት ቀርቶ ሊያስቡት በማይቻልበት ሁኔታ የማይታወቅ ድልን ተጎናጽፈው ፤ አድዋን የታላቋ ኢትዮጵያ እና የጀግኖች ህዝቦቿ ታሪካዊ ቅርስ ሆኖ እንዲፃፍ አደረጉ። ያንን ድልና ተጋድሎ ስንዘክር ድሉ ለአሁኗ ኢትዮጵያ ያለውን ፋይዳ እና በራስ ለመተማመናችን መሰረቱ እንደሆነ መረዳትና ማስረዳት ነው።

በእቴጌ ጣይቱ ብጡል እምቢ ባይነት፣ በወታደራዊ አዛዦቻቸው በራስ መተማመን ፤ በመላ ኢትዮጵያውያን ጀግንነት እና በዳግማዊ አጼ ምኒልክ መሪነት የተካሄደው የአድዋው ድል በባርነት ቀንበር ስር ለሚማቅቁ በመላው አለም ለሚገኙ ህዝቦች የተሰጠ ስጦታ ነው ብንል ያንስበታል። ከ15 ቀን በላይ በዘለቀው የአድዋው ጦርነት 5,000 የሚገመቱ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን መስዋዕት ሲሆኑ ሌሎች 8,000 ቆስለዋል። ከወራሪው የኢጣሊያ ጦር ሁለቱ የጦር አዛዥ ጄኔራሎችን ጨምሮ 7,000 የሚጠጉ ሰዎች ሲሞቱ 1,500 ቆስለዋል 3,000 ደግሞ ተማርከዋል። እንዲሁም ሁሉንም መድፍ እና 11,000 ጠመንጃዎች፤ መሳሪያቸውን አስረክበዋል። ድሉ በጣም አስደንጋጭ ከመሆኑ የተነሳ ዋና ዋና የአውሮፓ እና የአሜሪካ ጋዜጦች የፊት ገፅ ሽፋን ተሰጠው ።

በጣልያን የሚታተሙ ጋዜጦችም ሳይቀር ቪቫ ሚኒሊክ ብለው እስከመጻፍ ደረሱ ፡፡ በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ያሉ ጥቁሮች በኩራት አንገታቸውን ቀና ሲያደርጉ ቅኝ ገዢዎች መፃኢው ግዜ ምን ሊሆን እንደሚችል ባለማወቅ እና በስጋት አንገታቸውን እንዲቀልሱ አስገደዳቸው።አድዋ 1888 ዓ.ም፡፡

ኢትዮጵያ በታሪክ ሉዓላዊት ሀገር ሆና የኖረችው ለክብርና ለማንነታቸው ቀናኢና ጠንካራ መሰረቷ እንዳይነወጥ ፍላጎት የነበራቸው ከሁሉም አቅጣጫ የጎረፉ ህዝቦቿ በከፈሉት ከፍተኛ መስዋዕትነት ነው። ሀገር ወዳድ እና ቆራጥ ዜጎች በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩት ለእናት ሀገራቸው ለመሞት ዝግጁ ሆነው ሲዘምቱ ለራሳቸው አልሳሱም።ለሀገራቸው ህይወታቸውን ከመስጠት አልተቆጠቡም፡፡ በተለይም በዘመነ መሳፍንት ተብሎ በሚጠራው (1769-1855) ኢትዮጵያ በበርካታ ክልሎች ተከፋፍላ ውጤታማ የሆነ የማዕከላዊ መንግስት ቁጥጥር በሌለበት ወቅት፣ አብዛኛው ህዝብ መሬቱን እየተነጠቀ በፊውዳል ገዥዎች ስር ሎሌ ሆኖ እንዲያገለግል በመደረጉ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ይህን ባለመቀበል በተደረጉ የእርስ በርስ ጦርነት አልቀዋል። ኢትዮጵያውያን አራቱም የሀገሪቱ ክፍሎች ያለ ምንም ልዩነት ለከፍተኛ ስቃይ ተዳርገዋል። የሆነው ሆኖ፣ ምንም ይሁን ምን ኢትዮጵያውያን በብሔራዊ ሉዓላዊነታቸው ጨርሰው ተደራድረው አያውቁም። በአድዋ ላይ ለትውልድ የሚያኮራ ትሩፋት ያስቀረ ልዩ ድል እንዲቀዳጁ ያስቻላቸውም የዚህ ዓይነቱ ቆራጥ የኢትዮጵያ ህብረብሔራዊነት ዓይነተኛ መገለጫ ባህሪ ነው።



ለዓድዋ ድል እና ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እውቅና በመስጠቱ በርካታ የአፍሪካ እና የላቲን አሜሪካ ሀገራትም ጭምር ባለሶስት ቀለም (አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ) በሰንደቅ አላማን የነጻነት አርማ አድርገው እንዲቀበሉም ሆነ፡፡ በተለይ አፍሪካውያን ከቅኝ ግዛት ለመላቀቅ ባደረጉት መራራ ትግል ነፃነታቸውን በመቀዳጀታቸው፤የፓን አፍሪካን ንቅናቄ መጠናከር፤እሱን ተከትሎም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሰረት ገፊ ምክንያት ሆነ፡፡ ለዛም ነው ሰንደቅ አላማችን ለአፍሪካ - አሜሪካውያን የነፃነትና እኩልነት መለያ ተደርጎ እንዲወሰድ ያስቻለው፡፡ ለዛም ነው ኢትዮጵያ በታሪክ መዝገብ ልዩ ቦታ እንዲሰጣት ያደረገው። ያ እንደተጠበቀ ሆኖ ልናጠፋውና ልንፍቀው በማንችለው የግል ተረኮቻች ተጠምደን ለዘመናት እርስ በእርስ በመናቆራችን ድሉን በአግባቡ ባለመረዳት በታሪክ ውስጥ ራሳችንን ጠልፈን ለመጣል የተጓዝንበትን መንገድና ርቀት አሳይቶናል ፡፡ በዚህ በኛ ዘመን ኢትዮጵያ በጥቁር ህዝቦች ዓይን ያላትን አርማ ፍቀን ጥፋት ሰርተናል ፡፡ ከምንትነት ወደ ኢምንትነት ቁልቁል ራሳችንን ጥለናል።አሁንም የገነባነውን እሴትና የባህል ብሎም የስነልቦና ልህቀት እንዲሁም ድሉ የሚጠይቀውን ተግዳሮት ተቋቁሞ የሚያከብር ስነምግባርን ካልተላበስን በታሪክ ሚዛን ቀለን መገኘት ብቻ ሳይሆን ታሪክ ራሱ ክፉኛ ይፈርድብናል።

በአሁኑ ጊዜ ለጋራ ራዕይና ግቦቻችን መሳካት ፤ የቀደመ አብሮነትና መተሳሰብ ፤ከማንም ያልወረስነው የራሳችን ማንነት ፤ ባህልና ትውፊቶቻችን እንዲጠበቁ በጋራ መቆም ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር ወሳኝ እና አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ላይ እንገኛለን ። በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በባህል፣ በቋንቋ እና በፖለቲካዊ ልዩነቶች ላይ ተመስርቶና ተቧድኖ ከመሰነዛዘር ባለፈ ጀግኖች አባቶቻችን ያሳዩትን ተመሳሳይ የሀገር ፍቅር ማሳየት ብሎም ዘመኑ የአድዋ ዘማችነት ቁርጠኛ የመንፈስን መላበስ ይጠይቃል ። ለዘመናት በጋራ ተስማምቶ ሲኖር ፤ የሀገሩን ግዛታዊ አንድነት ለማስጠበቅ ከፍተኛ ዋጋ የከፈለን ኩሩ ህዝብ ለማይጠረቃው የግል ፍላጎታቸው መጠቀሚያ ሊያደርጉት ከሚቋምጡ ግለኞች ራስን በማቀብ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትውልድ አገሩን መረጋጋትና አንድነት ከሚያናጉ ድርጊቶች ሊጠበቅ ይገባል። በአለም ላይ ላሉ ጥቁር ህዝቦችን በጀግንነት እና በድል አድራጊነት ግንባር ቀደም ምልክት በመሆን እንዲሁም ነፃነትን የሚሹትን ሁላ በማዋሃድ ያደረጉት አስደናቂ ስራ በምናባዊ ህልመኞች ጉዞና ተረክ የነበረው እሴት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ሊወድቅ አይገባም። የዓድዋ ድል ከኢትዮጵያ አንድነትና ህልውና ያለፈ የላቀ ህብረተሰባዊ ትስስር የተጠናከረበትና የታየበት በዘመን ግርዶሽ የማታጠፍ መራራ ሀቅ ነው።

ባለፉት አምስት አስርት ዓመታት ውስጥ በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ባላዋቂ ደመሞቃት የፖለቲካ ልሂቃን ተቀስቅሰው ደም አፋሳሽ ግጭቶች ውስጥ ተዘፍቀው በሺዎች በእስር ቤት ውስጥ ታጉረው ቀሪዎቹ ወደ ባህር ማዶ ለመሰደድ ተገደዋል። የጥላቻ ፖለቲካ ያሰከራቸው ባደረጉት እረፍት አልባ ምክንያት የለሽ ቅስቀሳ ያስከተላቸው ጠባሳዎች እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያን እያንገላታ ነው። በፖለቲካው ምህዳር ውስጥ ያሉ ሁሉ መልካም አጋጣሚዎችን የሚጠባበቁ፣ በሰለጠነ ውይይት ሳይሆን ልዩነቶችን በሃይል መፍታት የሚመርጡ፣ ለሀገራዊ ጥቅም ደንታ የሌላቸው እና በስልጣን ጥማት የታወሩ ግለሰቦችና ቡድኖች በዝተው የሚታዩበት ግዜ ላይ ደርሰናል። ለረጅም ጊዜ ተቻችለውና ተስማምተው የምኖሩባት ሀገር እንዳልነበረች ዛሬ በጦር አውድማነት እየተቀየረች ነው። ዓለም የዓድዋ ድልን እያከበረ ባለበት በዚህ ወቅት፣ ቅድመአያቶቻችን በደማቸው አፅንተው ያቆዩትን መሠረታዊ እሴት የሚቀንሱና አገሪቱን የሚያዋርዱ ክስተቶች እየታዩ ነው። እስከ መቼ ነው ይህን መታገስ የሚቻለው? በአስቸኳይ መፍትሄ እስካልተገኘ ድረስ መዘዙ ተራ በተራ የሁሉንም ቤት ማንኳኳቱ የማይቀር ነው። አልተጠቀምንበትም ወይም በእጃችን የነበሩ አማራጮቻችንን በቅጡ አልተገነዘብንም እንጂ የታሪክ ጸሀፍት እንደሚሉት የአድዋ ድል በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መሠረታዊ የለውጥ ምዕራፍ ነበር። ሆኖም ያንን ምዕራፍ በአግባቡ ልንጠቀምበት ባለመቻላችን ዛሬ ለደረስንበት ውጥንቅጥ የራሱን አበርክቶ አሳርፏል፡፡ ያም ሆኖ በማይታበል ሀቅ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የጀግንነት እና የነፃነት አርማ ሆናለች፣የክብርና የተስፋ መሰረት ሆናም የውርደት ወረራ ሰለባ ለሆኑ እና "በተገዥነት" መዳፍ ስር መልስ ፍለጋ ላይ ለነበሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አፍሪካውያን ምሳሌ ሆና አገልግላለች። እናም ውለታዋን ያልዘነጉ ሀገራት የፀረ ቅኝ ግዛት ትግል ካደረጉ በኋላ ኢትዮጵያን አፍሪካውያን የአህጉራዊ ድርጅታቸው መቀመጫ እንድትሆን መረጡ። ስለዚህ የአድዋ ትሩፋትን በሚያረክስ እኩይ ነገር ላይ ተጠምዶ መዝለቅ አሳፋሪ ነው።ዛሬ የውጭ ወረራን መመከት ይቅርና ልዩነቶቻችንን በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመፍታት ያለው ድፍረት እየሸሸን ነው።ምክንያታዊነት ተሰውሮ ጎራ ለይቶና ተቧድኖ የተደረገው እሰጣገባና ብሽሽቅ የፈጠረልን አንዳች ፋይዳ አልበረም ወደፊትም ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ አሁን ላይ የመጣንባቸው መንገዶች ምን ያህል አስቀያሚና ውስብስብ እንደሆኑ ከተረዳን ለቀጣዩ ትውልድ የሚጠቅም ነገር ላይ አተኩረን መስራት እንደሚኖርብን ለአፍታ መዘንጋት የለብንም፡፡ ዛሬ በምንኖርበት ምድር አሜሪካ የጥቁሮች የነፃነት እና እኩልነት ተጋድሎ መታሰቢያ ታላቅ ቦታ ተሰጥቶት ወሩን ሙሉ ይከበራል ፡፡ ይታወሳልም፡፡የዚህ መሰረቱ ኢትዮጵያ እንደሆነችም ለማሳያነት ሰንደቋን ከፍ አድርገው ያውለበልቡታል፡፡ ዘመንን ተበድሮ መውቀስ ብዙም ፍላጎቴ አይደለም ፡፡ ሆኖም ግን ለንጽጽር ያህል አያቶቻችን የጣሉት መሰረት ሊጠበቅ ባለመቻሉ አባቶቻችን እርስ በእርሳቸው መግባባት ባለመቻላቸው ችግሮችን ተነጋግሮ በጠረዛ ዙሪያ መፍታት ተስኗቸው አንድ ትውልድ እንዲጠፋ ምክንያት ሆነ፡፡ በትውልድ መካከል እየተፈጠረ ያለው ክፍተት ከመጥበብ ይልቅ በአመዛኙ እንዲሰፋ መደላድል ሆነ፡፡ ሀገር ውስጥ በሚያድገው የስነ ልቦና ልህቀት ልክ እዚህ የተወለዱት ልጆቻችን አልያም በልጅነታቸው መጥተው እድገታቸውን እዚህ ያደረጉ ኢትዮጵያውያን ልጆችን እኩል ከኛ ጋር የሚስተካከል አልያም ተቀራራቢ የሆነ በራስ የመተማመም መንፈስ ውስጣቸው አለ ወይ ብለን ብንጠይቅ ፤ በዚህ ሀገር ባህልና የኑሮ ዘይቤ የጎለመሱት የሀገሬውን ስነልቦና መላበሳቸው የግድ ይሆንና በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ ህዝቦች ዘንድ ለተፈጠረው የስነልቦና ተፅዕኖ ተጋላጭ እንደማይሆኑ ደፍሮ መናገር አይቻልም የሚለው የቤት ስራችን እደሆነ በማስመር የአድዋ ድልን ስናከብር አገራዊ አንድነትንና ትብብርን በማጠናከር በታሪካችን ውስጥ የከበረ ገድል ለመስራት ቆርጠን መነሳት እንዳለብን በመረዳት ነው።ለትውልድ ቀናኢ ሆኖ መዝለቅ ከአንድ ኩሩና የነጻነትን ጣእም ከሚረዳ ሕዝብ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

## መልካም የአድዋ የድል በዓል!

... ከገፅ 13 የዞረ አድዋ እና ምርጫ...

ይህ የናይጄሪያ ወቅታዊ ሁኔታ ምን ያህል አሁን አገራችን ኢትዮጵያ ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታን እንደሚገልጽ የጥናቱን መደምደሚያ በመጥቀስ ( ግርድፍ ትርጉም-ዋናው የናይጄሪያውን አንድነት ተግዳሮት ቅኝ ገዥዎች የፈጠሩት የጎሰኝነትና የባህል ድንበር ሳይሆን ናይጄሪያውያን ራሳቸው የፈጠሩት ቅኝ ገዥነት ነው) ዶ/ር ይርጋ ገላው ስምምነታቸውን ይገልጻሉ፡፡ “so relevant to creation of native colonialism in Ethiopia” በማለት፡፡

አሁን ያለው የኢትዮጵያ አገረ-መንግሥት አስተዳደር ምን ያህል የቅኝ ገዥዎች መንፈስ የተጫነውና የአድዋ ድልን ያራከሰ እንደሆነ ከላይ ከቀረበው የናይጄሪያ ተሞክሮ መረዳት ይቻላል፡፡ግን እንዴት የአድዋ ድል ባለቤት ሆነን እዚህ ውስጥ እራሳችንን አገኘነው?

የ27 ዓመቱ የሕወሃት-ኢህአዴግ የአገረመንግሥት ሥርአት “የነባር-መጤ” ማንነትን መሠረት ያደረገ ትርክት በማንበር ኢትዮጵውያን በአድዋ ያገኙትን አንጸባራቂ የአንድነት ድል በማራከስ ለዘመናት ተዋልደው የኖሩትን ሕዝቦች ለማያባራ ግጭት ዳርጎን “ሸሸ፤ ወይስ አፈገፈገ”? ይህ ትርክት ጀግኖቻችንን እንኳን በጋራ እንዳናከብር የብሔር አጥር አበጅቶ ያናቁረናል፡፡ የዚህ ሥርአት ወራሽ የሆነው ተረካቢው ብልጽግናም አሻግራችኋለሁ ብሎ ቃል ቢገባም ወደነበርንበት እንዳንመለስ የሚያደርግ ዋስትና እስካሁን ከቃል ባለፈ አላሳየንም፡፡

ይህንን ሁኔታ ለመቀየር አሁንም ከፊታችን ምርጫ አለን፤ ምርጫዎቹም በዋናነት ያለፈውን ሥርአት እንዳለ ማስቀጠል፤ ጥገናዊ ለውጥ፤ ማካሄድ ወይም ፖለቲካዊ ሥርአቱን ከጎሳዊ ማንነት በማላቀቅ ዜጎች የብሔር፤ የሃይማኖትና ሌሎችም ማንነቶቻቸውን በማክበር እኩል የሚታዩበት ዜግነትን መሠረት ያደረገ ፖለቲካዊ ሥርአት መፍጠር ናቸው፡፡እኛ ምንኛው ውስጥ ነን?

የአድዋ ድል በነፃነትና በባርነት መካከል በተደረገ ምርጫ የተገኘ፤ የደም ዋጋ ተከፈለለት ድል ነው፡፡ ዛሬም ያለው ምርጫ በአገር በቀል የባርነት ሥርአት እና በዜጎች ፈቃድ በሚመሠረት ሥርአት መካከል የሚደረግ ነው፡ ፡ አንድ ምሁር እንዳሉት “የአድዋ ድል ከባርነት አስጥሎ እንደሰው አስከብሮናል የዘንድሮው በራሳችን ከራሳችን ጋር የምናደርገው ምርጫ ደግሞ ከታሰርንበት የመለያየትና ራስን የመጨቆን አባዜ አውጥቶ የሰውነት ክብራችንን የምናስመልስበት ሊሆን ይገባል::”

ታዲያ አድዋ እና ምርጫ አይገናኝም ትላላችሁ?

እድሜ ለአባቶቻችን በኩራት መንፈስ እነሆ 129 ዓመታት አሳለፍን፡፡

መልካም የአድዋ ድል በዓል ተመኘሁ

## አድዋና ኢትዮጵያዊነት ከገፅ 9 የዞረ

የኢትዮጵያዉያን ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽን (Ethiopian World Federation) ጸረ ፋሽስት እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ከነበሩት ማህበራት ተጠቃሽ ነው።

የአድዋ ድል እና ኢትዮጵያዊነት በአሜሪካ ውስጥ የነበረውን የነጻነት እና እኩልነት ትግል ከማቀጣጠል ባለፈ አድዋ በአውሮፓውያን ቅኝ ገዥ ተስፋፊዎች ላይ በአፍሪካ የተመዘገበ ታላቅ ድል በመሆኑ በአፍሪካ የተቃውሞ እና የነጻነት ትግል ውስጥም ታላቅ ምዕራፍ የሚሰጠው ነው። አፍሪካውያን ከቅኝ ግዛት ለመላቀቅ ባደረጉት ትግል ውስጥ የአድዋ ድልን እንደ ነጻነት ቀንዲል ተጠቅመውበታል። በመጨረሻም የአፍሪካ ሃገራት ከቅኝ ግዛት በ1960ወቹ ሲላቀቁ የኢትዮጵያን ባንዲራ የነጻነት እና የድል አርማ መሆኑን በመገንዘብ ከ30 በላይ የሚሆኑ ሃገራት ሰንደቅ አላማቸው አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለማት እንዲኖረው አድርገዋል። በአጠቃላይ አድዋ የነጮችን የተስፋፊነት ቅዠት የደረመሰ ድማሚት እንደመሆኑ መጠን በመላው አፍሪካ ድንበሮች ያስተጋባ፣ እስከ ካሪቢያን እና አሜሪካ ድረስ ትኩረትን የሳበ በተለይም አፍሪካውያን በአሸናፊነት እና በመተማመን መንፈስ ለነጻነታቸው እንዲታገሉ፣ እንዲሁም በመላው ዓለም ነጻነት አጥተው ለነበሩ ጥቁር ህዝቦች ተስፋ እንዲሰንቁ ያደረገ በመሆኑ ዓለም አቀፋዊ ፋይዳው የጎላ ነው። ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ እና ሌሎች የታሪክ ድርሳናት የተጠቀሰች



ጥንታዊት ሃገር በመሆኗ በጥቁር ህዝቦች ምናብ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተጽፋ የኖረች ብትሆንም በአጼ ምኒልክ እና እቴጌ ጣይቱ የተመራው የአድዋ ጦርነት ለኢትዮጵያዉያን ባቀዳጀው ድል ምክንያት የጥቁር ህዝቦች በሙሉ ሃገሪቷን የነጻነት እና የሉዓላዊነት ተምሳሌት አድርገው እንዲመለከቷት ምክንያት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ጥቁር ህዝቦችን በአንድነት አስተሳስሮ ከቅኝ ግዛት ለመውጣት እና ከዘረኝነት ለመላቀቅ ባደረጉት ትግል ውስጥ ትልቅ ሚና ተጫዉቷል።

**ክብር ደምና አጥንታቸውን ለከሰከሱ ጀግኖች አባቶቻችን ይሁን!**



# አድዋ እና ምርጫ




ይህን ርዕስ አይቶ ደግሞ አድዋ እና ምርጫ ምን አገናኛቸው ?ብሎ ግር ቢሰኝ አይገርምም እኔም ይህ ግርታ ተሰምቶኝ ነበር ፡፡ ግርታው ግን ምንም ያህል ከእኔ ጋር አልቆየም፤ እንዴ ሕይወት በምርጫ የተሞላች አይደለች እንዴ? የሚል ሌላ ጥያቄ አቀረበልኝ እኔም በአዎንታ መልሼ ቀጠልኩ፡፡ምርጫዎቻችን አንዳንድ ጊዜ ወደን ፈቅደን፤ አንዳንዴም የውዴታ ግዴታ ይሆኑብናል፤ በየትኛውም ሁኔታ ግን የመምረጡ ውሳኔ የራሳችን ነው ፡፡

የአድዋ ድል የሁለቱ ምርጫዎች ተዋሕዶ ልንለው እንችላለን፡፡ የአድዋ አንጸባራቂ ገድል ባለቤቶችና ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነፃነት ተምሳሌት ያደረገን የምርጫችን ውጤት ነው፡፡ ምናልባትም የውዴታ ግዴታ ምርጫ ልንለው እንችላለን፡፡ ይህ የሚያሰኘው ግን ጦርነቱ ወደንና ፈቅደን ያልገባንበት መሆናችንን ስናስብ ነው፡ቢሆንም ግን በቅኝ የመገዛት ምርጫ ነበረን፤ ነገር ግን ፈቅደን ወደን እንድንገባ ያደረገን ለነጻነታችን ያለን ቀናዒነታችን፤ ከባርነት በደማችን ነፃነትን መምረጣችን ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን ከሌሎቹ ተመሳሳይ የአውሮፓውያን የቅርምት አጀንዳ ከነበሩ ሕዝቦች የሚለየን፤ ይህንን በአፍሪካውያንና በመላው የጥቁር ሕዝብ ዘር ላይ የተቃጣውን የባርነት አዋጅ እምቢ ብለን በአንድነት በመቆም ወራሪውን የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ለመመከት በመምረጣችን ነው፡፡

አባቶቻችን ከአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናት የንጉሣቸውን የክተት ጥሪ ተቀብለው (ውስጣዊ ቁርቁሳቸውን ወደ ጎን በመተው)፤ ደማቸውን አፍስሰው አጥንቶቻቸውን ከስክሰው ባቆዩልን አገራችን ዛሬ ቀና ብለን እንድንሄድ፤ በመላው ዓለም ለሚገኙ ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ፋና ወጊ ሆነን እንድንታይና ጠንካራ የአይበገሬነት ሥነልቦና እንድንላበስ አድርጎናል፡፡ ይህንን መንፈስ እንድንላበስ ያደረገን ድል ለእጅጋየሁ ሽባባው ጥልቅ የአድዋ መረዳት ምንጭ ሆኗል፡፡

የተሰጠኝ ሕይወት ዛሬ በነፃነት  
ሰው ተከፍሎበታል ከደምና ከአጥንት  
ስንት ወገን አለቀ ለነፃነት ክብር  
ትናገር አድዋ ትናገር ትመስክር  
ትናገር አድዋ ትናገር አገሬ  
እንዴት እንደቆምኩኝ ከፊታችሁ ዛሬ::

በውጭ ወራሪዎች የተቃጣብንን የባርነት ድግስ በተደጋጋሚ በአንድነት በመቆም እምቢኝ ያልነውን ያህል በአገር በቀል ጨቋኞች የደረሰብንን የመከራ ቀንበር ለመሸከም ያሳየነው ትዕግስት ወይም ቸልተኝነት አሊያም ጭቆናን መለማመድ ግን ዛሬም ድረስ ያልተፈታ እንቆቅልሻችን ይመስለኛል፡፡

እውነት ነው ቅኝ ገዥዎች አፍሪካውያንን ለመግዛት የሚያስችላቸውን ስልት ነድፈው እርስ በእርሳችን እንድንጠራጠር የጎሳ፤የሃይማኖት፤የባህል እና የመልክአ ምድር ድንበር አበጅተውልናል፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ ናይጄርያ አሁን ያለችበትን ነባራዊ ሐቅ ያጠኑ ምሁራን መጥቀስ (ምንም እንኳን በቅኝ ግዛት ባንገዛም)፤አሁን ያለንበትን ሁኔታ ለማንፀር ይጠቅመናል በሚል እዚህ ወስጀዋለሁ፡፡ (ትርጉም የራሴ)


የቅኝ ገዥዎች አስተዳደር በመሬት ላይ የሚታይ ድንበር (ክልል) በአገሪቱ ሕዝቦች መካከል አበጅተዋል፡፡ ይህም አገሪቱን ለመበዝበዝ አስችሏቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ሀብትን ለመቆጣጠር በሚደረግ የኃይል ክፍፍልና ሽኩቻ ማንነትን መሠረት ያደረገ ቁርቁስ አስከትሏል ባለፉት ዘመናት የነበሩ ማኅበረሰቦች በዚህ ትርጉም አልባ ድንበር ምክንያት የማይታረቁ ጠላቶች እንዲሆኑ ምክንት ሆኗል፡፡

ይሁንና በቅኝ ገዥዎች ምክንያት ከተፈጠረው የእርስ በእርስ ክፍፍል ይልቅ በ “አገር በቀል ቅኝ ገዥዎች” የሆነውና እየሆነ ያለው በቅኝ ገዥዎች የተጀመረው የብዝበዛ ሂደት የሚያስቀጥል ሆኖ ይታያል፡፡ ይህንን ሁኔታ ነው ምሁራኑ የናይጄሪያን ወቅታዊ ሁኔታን ለማስረዳት ካስቀመጧቸው ሦስት መተንተኛ እሳቤዎች፤ለእኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ የቀረበው እሳቤ “Native-settler identities” በግርድፉ የነባር-መጤ ማንነት ብለው የጠሩትን ለጉዳዬ አስረጅ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

ይህ የሶስተኛው ደረጃ በአፍሪካውያን ልሒቃን የተፈጠረና እስካሁንም የቀጠለው፤ ለህልውናውም ዘርን፤ ጎሳን እና ሃይማኖትን መሠረት ያደረገው እሳቤ የአገረ መንግሥት ግንባታ ምሶሶ በማድረግ አገራዊ አስተዳደሩን የሚቆጣጠሩ ሰዎች “ከየትኛው ወገን ተወለዱ የሚለው ዋነኛ መመዘኛ ሆነ፡፡ በዚህም ከነጻነት በኋላ ያሉ መሪዎች ቅኝ ገዥዎች ያሰመሩትን የጎሳና የሃይማኖት መስመሮች ለራሳቸው ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ አውለውታል::” ...ወደ ገፅ 12 ዞሯል

# “እኔ ሴት ነኝ ጦርነት አልወድም።”

ሔርሜላ አበበ



የአድዋ ጦርነት በ1888ዓም ሲካሄድ ለጦርነቱ መንስኤ ተደርጎ የሚጠቀሰው የውጫሌው ውል አንቀፅ 17 ላይ በአማርኛውና የጣሊያንኛው ፅሁፈት ትርጓሜ የተለያየ መሆኑ በወቅቱ ለነበሩት ንጉስ ዳግማዊ ሚኒሊክ፤ እቴጌ ጣይቱ ብጡል እና በባለሟሎቻቸው ዘንድ የፅሁፉ ጭብጥ ስላልተዋጠላቸው መልእክተኞቻቸውን ልከው ማብራሪያ ይጠይቃሉ፡፡ የፊደል ግድፈት ሊያመጣ ወይም ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ ኢትዮጵያውያን በደንብ ያውቁታል፡፡

ቆዳ አለዝበው ብራና ፍቀው ፊደልና ቁጥር ቀርፀው የራሳቸው የሆነ ባህልና ስርዓት ዘርግተው ለዘመናት ለቆዩ ህዝቦች የፊደል ግድፈት ሊያመጣ የሚችለውን ወይም ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ የሊቃውንት ጉባኤ ዘንድ መሄድ ሳያሻቸው አንብበው የመረዳት ክህሎታቸው ከደርዘን በላይ አማካሪና ባለሟሎች ካሏቸው የአውሮፓውያን የዘመኑ ገዥዎች ቢያይል እንጂ የሚያንስ እውቀትና ብልሀት አልነበራቸውም፡፡ እናም ይህንን ጠንቅቀው ቢረዱና ቢጠረጥሩ ነብይ አልያም ጠንቋይ አያሰኛቸውም፡፡ከዚያ ይልቅ ሊመጣ የሚችለውን ጠንቅቀው መረዳት ማወቅና ማስተንተን መቻላቸው የቀደመው የሀገሪቱ ዘመን ጠገብ እውቀት ጥበብና ክህሎት መዳበር ውጤት ተደርጎ መመልከት የሚያስችል ያልነጠፈ ፤ ዘመን ያልሻረው ከቀደሙት ምንጮች የተቀዳ ነው የሚያስብል እንጂ በከንቱ ውዳሴነት የሚጠቀስ አይደለም፡፡

ለዛም ነው የውጫሌው ውል ‹‹አንቀጽ 17 በአማርኛ “የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከአውሮፓ ነገስታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ መንግስት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል” የሚል ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙም የኢትዮጵያ መንግስት ከፈቀደ ወይንም ከፈለገ በኢጣሊያ በኩል ከውጭ መንግስታት ጋር ግንኙነት ማድረግ እንደሚችል ይጠቅስና የአንቀጹ የጣሊያንኛ ትርጉም ግን “የኢትዮጵያ መንግስት ከውጭ ሀገር መንግስታት ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግስት አማካኝነት ማድረግ ይገባዋል” የሚል ነበር፡፡ ይህም የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት በቀጥታ በጣሊያን በኩል እንዲከናወን የሚያስገድድ ነበር፡፡ በአንቀጹ በጣሊያንኛ በመቀየር የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመገርሰስ የጣልያን ሞግዚት እንድትሆን ቀዳዳ እያበጀች ነው ብለው ነገሥታቱ እና መኳንንቱ ስለተገነዘቡ የውጫሌ ውልን እንደማይቀበሉት አሳወቁ፡፡

የጣሊያን መንግስት ውሉን ለማፍረስ አሻፈረኝ በሚልበት ጊዜ፣ የውጫሌ ውል እንዲፈርስና ኢትዮጵያ ለማይቀረው ጦርነት እንድትዘጋጅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካበረከቱ ግለሰቦች መካከል የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ሚስት የሆኑት እቴጌ ጣይቱ ብጡል እንደነበሩ ታሪክ ይናገራል፡፡ እቴጌዋ “እኔ ሴት ነኝ፣ ጦርነት አልወድም፡፡ ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከምቀበል ጦርነት እመርጣለሁ” ሲሉ በልበ ሙሉነት በንጉሱና በባለሟሎቻቸው ፊት ተናገሩ፡፡ በዚህም መነሻነት ጦርነቱ አይቀሬ ሆነና ምታ ነጋሪት ክተት ሰራዊት ተባለ ፡፡

ከአራቱም የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት ለሚገኙ ሁሉ ወረኢሉ ከተህ ላገኘህ ሲሉ ዳግማዊ ሚኒሊክ ማዘዛቸውን በየአውራጃው በሚገኙ ባለሟሎቻቸው አማካኝነት ሁሉም መልክቱ እንዲደርሰው አስደረጉና ወደጦርነቱ ቦታ አቀኑ፡፡እቴጌም የሴት አርበኞችን በማሰለፍ ወደውጊያው ንጉሱን ተከተሏቸው ፡፡

ባለሟሎቻቸውን አሰልፈው እሳቸው ቤት እልፍኛቸውን ያስጠብቃሉ ተብሎ ሲጠበቅ እልፍኝ ጓዳቸውን ጥለው በቃላቸው “እኔ ሴት ነኝ፣ ጦርነት አልወድም፡ ፡ ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከምቀበል ጦርነት እመርጣለሁ”ያሉት እቴጌዋም ቃላቸውን ጠብቀው በወንዶቹ ቦታ ተገኙ ፡፡ በሌላ አነጋገር ጦርነቱን መረጡ ፡፡ ቀኑን በውጊያ ሌሊቱን በምግብ ዝግጅት ረጅሙን ግዜ በዚያው ሰነበቱ፡፡ጦርነቱ ሲበረታ ለመሸሽ የሚንደረደረውን ዘማች ከኋላ እየተከተሉ ንጉሱ በጦርነቱ ውሎ ሳይገባ ወዴት ልትደርሱ ነው ? ነውርም አይደል! እያሉ የፈራውን እያበረቱ ወደ ጦርነቱ ይልኩ ነበር ፡፡በርክሌ እንደፃፈው እቴጌዋ በጦር አዝማችነት ይታወቁ እንደነበርና በስራቸው የሚታዘዙ ሶስት ሺ ተዋጊዎችና አራት መድፈኞች እንደነበሯቸው ዘግቧል፡፡ በመቀሌውና በአድዋው ጦርነት አብረዋቸው ከነበሩት ሌሎች ሴቶች ጋር ሆነው በጦርነቱ መካከል ተገኝተው አዋግተዋል፡፡

በተለይም ጄነራል አልበርቶኒ ድል በሆነበት እንዳ ኪዳነ ምህረት አካባቢ ደርሰው የሰሩትን ስራ ፀሀፊ ትእዛዝ ወልደአረጋይ እዲህ ሲሉ ፅፈውላቸዋል ፡፡ በዚህም ግዜ እቴጌ ጥቁር ጥላ አሲዘው አይነርግብዎን ገልጠው በእግርዎ ሲሄዱ ነበር፡፡ሴት ወይዛዝርቱም የንጉሰ ነገስቱም ልጅ ወይዘሮ ዘውዲቱም ደንገጡሮችም ተከትሎዎ ነበር፡፡የኋላው ሰልፍም እንደ መወዝወዝ ሲል ባዩ ግዜ ተናገሩ ‹‹አይዞህ አንተ ምን ሆነህል? ድሉ የኛ ነው በለው! አሉት›፡፡ ሰዉም የተናገሩትን ቃልና እቴጌይቱን ባየ ግዜ ሴት ሲያጠና ወንድ መሸሽ አይሆንለትምና ፀጥ አለ፡፡እቴጌም ነፍጠኞቹን በግራና በቀኝ አሰልፈው በዛ ቀን የሴቶችን ባህሪ ትተው እንደተመረጠ እንደጦር አርበኛ ሆነው ዋሉ፡፡የእቴጌም መድፈኞኞች እቴጌ በቆሙበት በስተቀኝ መልሰው መልሰው መድፍ ቢተኩሱ በመካከል የመጣውን የኢጣልያ ሰልፍ አስለቀቁት፡፡ንግስቲቱ እቴጌ ጣይቱ የመጀመሪያው ኢጣሊያዊ ድል የተደረገበት ቦታ ላይ ቆመው የተከተለውን ሰው ወንዱ በእርኮት ሴቱ በገንቦ ውሀ ያዙ ብለው አዘው ለተጠማውና ለቆሰለው ውሀ ሲያጠጡት ዋሉ፡፡እንኳን የኢትዮጵያ ሰው የኢጣልያ ቁስለኛ እንኳን ከዚያ ስፍራ የተገኘ እቴጌ ካዘዙት ውሀ አልቀረበትም፡፡ዘጠኝም ሰዓት በሆነ ግዜ ዳግማዊ የአፄ ሚኒሊክ ሰራዊት ቁስለኛውን የማረከው የጣሊያን ሰራዊት እየያዘ ይመለስ ጀመር ፡፡አፄ ሚኒሊክ ግን ከጦሩ ገና አልተመለሱም ነበረ ፡፡እቴጌም ሰራዊቱ ብዙ እየሆነ ሲመለስ ባዩ ግዜ ‹‹ንጉሱ ሳይመለስ ወዴት ትሄዳላችሁ ? የቆሰለውን ሰው እኔም ካለሁበት አሳርፉት ፡፡እናንተም ተመለሱ ፡፡ ብለው አሳረፉት፡፡ማለታቸውን ጠቅሰዋል፡፡


እቴጌ ጣይቱ ይህንን የጦር ሜዳ ውሎና ልበሙሉነት ደብቀው ሳይሆን አይቀርም ለጣሊያኑ መልእክተኛ እኔ ሴት ነኝ ጦርነት አልወድም ሲሉ የገለፁት፡፡ አልያም የሀበሻን ክንድ ለማሳየት ጣሊያንን ወደጦርነቱ ገፍቶ እንዲገባ ለማድረግ የተጠቀሙበት ዘዴም ሊሆን እንደማይችል ከራሳቸው ከንግስቲቱ ውጭ ማን ሊያውቅ ይችላል? አድዋ ዘርፈው የማይጨርሱት ቅኔ ነው የሚባለው ለዚህም ይደል ፡፡ እኔ ሴት ነኝ ጦርነት አልወድም ብላ ወደጦርነት የገባች እንስት ከጣይቱ በቀርስ በዓለም ላይ ፈልጎ ማግኘት ይቻል ይሆን ? እኔ እንጃ፡፡ብቻ ጦርነት የማትወድ ጦረኛ ሆና የተገኘችው ጣይቱና ጣይቱ ብቻ ናት፡፡ ስለሷ እያሰላሰልኩ አንድ ነገር በውስጤ ሲርመሰመስ ተሰማኝ፡፡ባሳለፍኩት ቅዳሜ ኢካን ባዘጋጀው የእራት ገቢ ማሰባሰቢያ ላይ ታድሜ የቀረበውን ዘጋቢ ፊልም አይቼ መስራትና መተባበር ብንችል ከዚህ በላይ ተቋትን መገንባት አንችልም ወይ ? ለዚህስ የሚሰንፍ ወላጅ እንዴት ሊኖር ይችላል ? የሚለው ሰቅዞ ያዘኝ፡፡ሴት ነኝ ጦርነት አልወድም ብትልም ቅሉ ጣይቱ በጦር ሜዳው ሰልፍ አሸናፊ ሆና እንደምትወጣ እርግጠኛ ነበረች፡፡ ምክንያቱም እሷ ኢትዮጵያዊ ነችና፡፡ታዲያ የኔ ዘመን አድዋን ሁላችንም ከተረባረብን አንድ አይደለም የተለያዩ የባህል ማእከላትን መገንበት እንዴት ሊሳነን ይችላል? እንግዲህ ለዚህ የሚጠይቀው ራስን እንደ ጣይቱ ልበ ሙሉ ማድረግ ነውና፤ሁላችንም ያን ልበሙሉነት እንላበስ እላለሁ፡፡

መልካም የአድዋ ድል በዓል!!











# Tihut Sebsiebe

“Forever United” is a powerful oil painting that embodies Ethiopia’s enduring struggle and aspiration for unity. At its center stands Yekuno Amlak, a pivotal figure in Ethiopian history, depicted with a commanding presence as he points toward a landscape of lush greenlands dotted with traditional huts, symbolizing the nation’s deep-rooted heritage. In his other hand, he firmly holds the neutral Ethiopian flag, representing unity beyond political and ethnic divisions. Surrounding him is a diverse group of individuals, each distinctly representing different regions of Ethiopia, their gazes following his direction with expressions of hope and determination. The painting’s composition leads the eye to the far left, where two modern buildings stand as the last human-made structures, signifying Ethiopia’s ongoing journey toward urbanization and progress. This visual contrast between the traditional and the contemporary reinforces the painting’s central theme—despite historical and ongoing internal struggles, Ethiopia’s strength lies in its ability to work together and embrace a shared future.

